# በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

## ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ለማቋቋምና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ረቂቅ ላይ የቀረበ አስተያየት

አዲስ አበባ

ጥቅምት 1996

# ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ለማቋቋምና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ረቂቅ ላይ

## በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የቀረበ አስተያየት

*ክፍል - 1 የማንዛቢ ማስጨበጫ ሀሳቦች*

### 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አስፈላጊነት መሠረታዊ መነሻ በሀገሪቱ ህገ-መንግሥት የተረጋገጡ መሰረታዊ የሰብዓዊ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶች ተፈጻሚነትን በቋሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሕጋዊ የማንነት መረጃዎችን ለመንግሥትና ለግለሰቦች በማስገኘት ዜጎች በአገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የልማት ሥራዎች ሙሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን መብትና ግዴታ ለማስጠበቅ ነው። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር በዓለማችን ረጅም ዕድሜን ያስቆጠረ ቢሆንም የምዝገባው ዓላማና የአሰራር ዘዴው ዘመናዊ መልክ በመያዝ በመንግሥት ህግ ተካቶ ዋንኛ የመንግሥት ተግባር የሆነው ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ነው።

በመሰረቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዋንኛ ተግባር መረጃ ማመንጨት ነው። ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚመነጩ መረጃዎችም በዋንኝነት ለህግ፣ ለህዝብ አስተዳደርና ለስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ፍጆታ ይውላሉ። በምዝገባ ሥርዓቱ የሚመዘገቡትና የሚሰበሰቡት መረጃዎች በግለሰቦች፣ በማህበረሰብና በመንግሥት ደረጃ በቅንጅት ጥቅም ላይ ለመዋል የሚያስችላቸው የአሰራር ስልት ተነድፎላቸዋል። ይኸም የአሰራር ስልት የሁለት የአመዘጋገብ ሥርዓቶች ጥምረት ውጤት ነው። እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠራር እነዚህ ሁለት ሥርዓቶች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት በመባል ይታወቃሉ። የእነዚህ ሁለት መረጃ ሥርዓቶች ጥምረት በዋንኝነት በህግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር፣ መረጃ አመዘጋገብና ፍሰት እንዲሁም የኦፕሬሽን ምሪት አደረጃጀት መመሪያ ዝግጅትና አተገባበር ይገለጻል።

በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን የማቋቋምና አስተዳደራዊ አደረጃጀቱን የመዘርጋት ተግባር በህግ መደንገግ የሚገባው ስለሆን በኢትዮጵያም በቅድሚያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ መዘጋጀትና በፓርላማው መጽደቅ ይገባዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በዘረጉትም ሆነ ባልዘረጉት ሀገሮች ባካሄደው ተከታታይ ጥናትና በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች እንዲጠቀሙባቸው ባወጣቸው በርካታ ቴክኒካዊ ሪፓርቶችና የአሰራር መመሪያዎች ላይ በአንድ ሀገር የምዝገባ ሥርዓት የህግ አቀራረጽ፣ የመረጃ አመዘጋገብና አጠንቃቀር የቴክኒክ አሰራሮች፣ መዋቅራዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀቶች ከየሀገሩ

ህገ-መንግስታዊ የህግና የአስተዳደር አደረጃጀት ጋር ተገናዝቦ መስራት እንደሚገባው በማስገንዘብ ከረጂም ጊዜ ጀምሮ ለአባል ሀገሮች መመሪያዎቹን ሲያስራጭ ቆይቷል (በዘርፉ በድርጅቱ የተዘጋጁ በርካታ የጥናት ሥራዎች በኮሚሽኑ ጽ/ቤት ይገኛሉ)። እነዚህ መመሪያዎች በተለይም ገና ሥርዓቱን ለመዘርጋት እያሰቡ ላሉ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮች ትልቅ እገዛ እንደሚያደርጉ ይታመናል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 103 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 180/1991 የተቋቋመው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የኮሚሽኑ ዓላማ በሚለው ሥር በአንቀጽ 4(2) ኮሚሽኑ "የሕዝብ እና የቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሰራበት መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ" እንደሚገባው ተደንግጓል። በመሰረቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ለፖለቲካ ሥርዓቱ አደረጃጀትም ሆነ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች የዕቅድ ዝግጅት፣ ለዕቅድ አፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር ተግባር ለማዋል በዋንኛነት ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ከሚገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ መደገፍ ይኖርበታል። በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ የተመለከተውን ሁለተኛውን የኮሚሽኑን ዓላማ መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ለዚህ ዓላማ መሳካት የተግባር መነሻ የሆነውን በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን (Civil Registration and Vital Statistics Systems) የመዘርጋቱን ቴክኒካዊ የዝግጅት ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት እውቅና የተሰጣቸውን በርካታ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች በአግባባዊና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣው የመረጃ አቅርቦት የአሰራር ስልት ለማስጠበቅ የሚቻለው በሀገሪቱ የኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶች ማቋቋም ሲቻል ብቻ እንደሆነ ጽ/ቤቱ ይገነዘባል። በዚህ ረገድም ጽ/ቤቱ በስነ-ህዝብ መረጃ አቅርቦት ዘርፍና በናሙና ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር ባለው የተካበተ ልምድ በመደገፍ በየክልል መስተዳድሩ የሚከናወኑትን ግለሰባዊ የህግ መረጃዎች አመዘጋገብና የመረጃ አቅርቦት ሥርዓቱን ለማስተባበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሀጉን ሀገር አቀፍ አልፎም ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲቀረጽ ለማድረግ ያደረገውን ዝግጅት በመንተራስ በተረበው ረቂቅ የኩነቶች ምዝገባ አዋጅ ላይ ሙያዊ አስተያየቱን በሁለት ክፍሎች በመክፈል ያቀርባል። በክፍል አንድ አጠር ባለና በተጠቃለለ መልኩ ስለኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሀሳቦች የተገለጹ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ በረቂቅ አዋጁ በተካተቱ አንቀጾች ላይ ዝርዝር ሙያዊ አስተያየት ቀርቧል።

## 1.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች

ወሳኝ ኩነቶች በሁለት መሰረታዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት ዓለም አቀፍ ዕውቅና ከተሰጣቸው መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። የመጀመሪያው ራሳቸው ወሳኝ ኩነቶቹ (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለበርካታ ዕውቅና ለተሰጣቸው መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መተግበር የአስተዳደር አፈፃፀም ሥርዓት ምንጭ መሆናቸው ነው። ይህንኑ መሰረት በማድረግ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ላይ በአንድ በኩል

የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ መመዝገብን በራሱ የሰብዓዊ መብት አድርጎ የደነገገ ሲሆን በሌላም በኩል እነዚህ ወሳኝ ኩነቶች ለመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መተግበር የአስተዳደር አፈፃፀም ሥርዓት ምንጭ በመሆን የሚኖራቸውን ወሳኝ ድርሻ ለይቶ ያስቀምጣል። ይህንኑ የወሳኝ ኩነቶች መመዝገብና የሰብአዊ መብቶችን ቁርኝት መሠረት የጣለው እ.ኤ.አ. በ1974 የፀደቀው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የስነ-ህዝብ የድርጊት መርሀ-ግብር ሲሆን በዚህ መርሀ ግብር መሠረት መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች በሁለት ምድብ ተከፍለው ቀርበዋል። እነዚህም በእያንዳንዱ አገር የመመዝገብ መብት ያላቸውና በተመዘገቡ የወሳኝ ኩነቶች አማካይነት ተፈጻሚ የሚሆኑ ሰብዓዊ መብቶች ተብለው ተከፋፍለዋል።

በእያንዳንዱ አገር የመመዝገብ መብት ያላቸው ወሳኝ ኩነቶች ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ሲሆኑ እያንዳንዱ አገር በአለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ መሠረት እነዚህን ኩነቶች የመመዝገብ ግዴታ ተጥሎበታል። በዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ /24/ ማንኛውም ህፃን እንደተወለደ ወዲያውኑ መመዝገብ እንደሚኖርበት፣ እያንዳንዱ አባል መንግሥትም በየዕለቱ በመወለድ የህብረተሰቡ አባል የሚሆኑ ህፃናትን የማህበረሰብ አባልነታቸውን፣ ማንነታቸውን በሚለይ የምዝገባ አሰራር በቋሚ የመንግስት ሰነድ መመዝገብ እንዳለበት ደንግጓል። በተጨማሪም በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ /7/ ህፃኑ ወዲያው እንደተወለደ የመመዝገብ፣ ስምና ዜግነት የማግኘት መብት እንዳለው ተመልክቷል። በዚህ ህጋዊ የመንግስት ሰነድ ላይ በመመሥረት ለተወለደው ህፃን ስለመወለዱና የማህበረሰቡ አባል ስለመሆኑ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትም ወዲያው እንደተወለደ መሰጠት እንደሚገባ የተደነገገ ሲሆን ይህም አሠራር ዘመናዊና አግባባዊ የህዝብ አስተዳደር ሥርዓት መርህ ሆኖ ተቀምጧል። በነዚህ የምዝገባ ሰነዶች ላይ በመመሥረት መንግስት ለዜጎቹ ወቅቱን የጠበቀ የህግ፣ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና ልዩ ልዩ የአስተዳደር አገልግሎቶችን የመስጠትና የመቀበል ግዴታውን እንዲወጣ የሚያስችል መሆኑና በዚህ ህጋዊ የልደት ምስክር ወረቀት አማካኝነት ህፃኑ በልጅነትና በቀሪ ዕድሜው የማህበረሰብ አባልነት መብቱን ለማስጠበቅና የዜግነት ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችለው ህጋዊ መረጃ ሆኖ እንዲያገለግል በተዛማጅ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተመልክቷል።

ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ /12/2 (a)/ የኮንቬንሽኑ አባል ሀገሮች ከሌሎች ተግባራት በተጨማሪ ቅድመ ወሊድ ሞትን እና የህፃናትን ሞት ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባቸው ይገልፃል። የሞት መመዝገብ መብት የህፃናትን ጤናማ አስተዳደግ ከማስፈን ጋር በተያያዘ ከመገለጹ በተጨማሪ ከሰብዓዊ መብቶች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ (ለምሳሌ ከመውረስ መብት፣ ከማህበራዊ ዋስትና ማስጠበቅ መብት፣ ...) የሞት መመዝገብ መብት አስፈላጊነት ተገልጿል። መንግሥት ለግለሰቦችና ለአካባቢ አስተዳደር የማህበረሰብ ክፍሎች የሚሰጣቸውን የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አገልግሎቶች አግባባዊውን አስተዳደር መሠረት አድርጎ ለመፈፀም በየዕለቱ በሞት ምክንያት ከህብረተሰቡ የሚለዩትን ሰዎች ከማህበረሰብ አባልነታቸውና ከመንግስት ሰነድ ለመሰረዝ የሞት ኩነት መመዝገብ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። መንግሥት ይህንኑ የሞት መከሰት መረጃ የህግና የአስተዳደር አገልግሎት ሰጪ አካላት እንዲያውቁት ከማድረግ በተጨማሪ የሟች ዘመዶች ህጋዊ የሞት መከሰት ማረጋገጫ መረጃ እንዲሰጣቸው/እንዲኖራቸው/ ማስቻል ግዴታው ስለሆነ ሞት የመመዝገብ መብት እንዲኖረው ተደርጓል። በሌላም በኩል ስለአንድ ሀገር

ወይም አካባቢ አስተዳደር የሞት መጠን ከነመንስኤው በማቀናባበር የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለማወቅና ተገቢውን የመከላከያ ዘዴ ለማዘጋጀት የሚረዳ መረጃ ለማጠናቀር የሞት ኩነት የመመዝገብ መብት እንዲኖረው ተደርጓል።

የጋብቻ መከሰት የሚያረጋግጠውን ህጋዊ መረጃ ተጋቢዎች እንዲሰጣቸው/ እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ይህንኑ የማህበረሰብ አባልነት መብታቸውን ለማስጠበቅና ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ጋብቻ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል መመዝገብ እንዳለበት በአለም አቀፍ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል። የጋብቻ ፈቃደኝነት፣ የጋብቻ ዕድሜ እና የጋብቻ ምዝገባ ኮንቬንሽን አንቀጽ /3/፣ ማንኛውም ጋብቻ የኩነቶች ምዝገባ እንዲያካሂድ ስልጣን ባለው የመንግሥት አካል መመዝገብ እንደሚኖርበት ይደነግጋል። በሌላም በኩል በሴቶች ላይ የሚደረጉ ልዩነቶች ማስወገጃ ዲክላሬሽን አንቀጽ /6.3/፣ ትንሹን የጋብቻ ዕድሜ የሚወስንና ጋብቻን መንግሥት ባቋቋመው የጋብቻ መዝገብ ሥልጣን ባለው አካል ለመመዝገብ የሚያስገድድ ህግ እንዲወጣ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል።

የሚፈርሱ ጋብቻዎች የተጋቢዎችን ህጋዊ አቋም ለውጥ የሚያስከትሉ ስለሆነ ይኸው ክስተት በመንግሥት እውቅና ተሰጥቶትና በመንግስት ሰነድ ተመዝግቦ ለመያዝ እንዲቻል፣ ይህንኑ የፍቺ መከሰት የሚያረጋግጠውን ህጋዊ መረጃ ተፋቺዎች እንዲሰጣቸው/እንዲኖራቸው በማድረግ ተፋቺዎችና ፍቺው የሚመለከታቸው የቤተሰብ አባላት በህጋዊ ሰነዱ የማህበረሰብ አባልነት መብታቸውን ለማስጠበቅ እንዲሁም ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል፣ ፍቺ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም የመመዝገብ መብት እንዳለው በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተመልክቷል። ይኸንኑ መርህ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ 843(IX) 1954 ፍቺ ወይም ህጋዊ መለያየት ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት መወሰን እንደሚገባውና ፍችው ህጋዊ ምዝገባ ሊደረግለት እንደሚገባ ይደነግጋል።

ከላይ በአጭሩ የተመለከቱት የኩነቶች ምዝገባ አስፈላጊነት መሰረታዊ ሀሳቦች መንግሥታት ኩነቶችን የመመዝገብ ግዴታ እንደተጣለባቸው በዓለም አቀፍ ህጋጋትና ስምምነቶች መገለጹን ለማመልከት የቀረበ ሲሆን በነዚህ በተመዘገቡት ኩነቶች አማካይነት ተፈጻሚ የሚሆኑ ሰብዓዊ መብቶች በርካቶች ናቸው። ከእነዚህም ቀጥሎ የተመለከቱት ዋንኞቹ ናቸው።

1. ስም የማግኘት መብት፣
2. ወላጆችን የማወቅ መብት፣
3. ዜግነት የማግኘት መብት
4. የጤና ጥበቃ አገልግሎት
   የማግኘት መብት፣
5. የቤተሰብ ጥበቃ የማግኘት መብት፣
6. የወጣት አጥፊዎች መብት፣
7. ትምህርት የማግኘት መብት፣
8. የጋብቻ መብት፣
9. ከግዴታ ጋብቻ የመጠበቅ መብት፣
10. ምግብ የማግኘት መብት

11. ልብስ የማግኘት መብት፣
12. ቤት የማግኘት መብት፣
13. ሥራ የማግኘት መብት
14. ንብረት የማፍራት መብት፣
15. የመውረስ መብት፣
16. የመፍለስ መብት፣
17. የጡረታ መብት፣
18. ሕፃናት የማሣደግ መብት፣
19. የመምረጥና የመመረጥ መብት፣

እነዚህ መብቶች በአንድ ሀገር አግባባዊ የልደት፣የሞት፣ የጋብቻና የፍች ምዝገባ ሥርዓትን በማቋቋም በሚገኙ ህጋዊ መረጃዎች አማካይነት ተፈፃሚ ይሆናሉ። ለምሣሌ ስም የማግኘት መብት፣ የዜግነት መብት፣ የወጣት አጥፊዎች መብት፣ የትምህርት ማግኘት መብት፣ የጋብቻ መብት፣ የምግብ ማግኘት መብት፣ የልብስ ማግኘት መብት፣ ቤት የማግኘት መብት፣ ሥራ የማግኘት መብት፣ ንብረት የማፍራት መብት፣ የመውረስ መብት እና የመምረጥ መብት በዋንኛነት ከልደት ምዝገባ በሚገኘው ሕጋዊ ምስክር ወረቀት አማካይነት ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው። እንዲሁም የጤና መጠበቅ መብትና የልጆች ማሣደግ መብት ከሞትና ልደት ምዝገባ በሚገኙት ሕጋዊ መረጃዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ። ሌላው የቤተሰብ ጥበቃና አስገድዶ ማግባትን የመከላከል መብት የሚገኘው ከጋብቻና ልደት ምዝገባ በሚገኙት ሕጋዊ መረጃዎች አማካይነት ነው።

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቀረቡ በርካታ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ስምምነቶችን በመቀበል መፈረሙዋ ይታወቃል። እነዚህን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችንና ድንጋጌዎችን አግባባዊ አሰራሮችን በመከተል ተግባራዊ ለማድረግ ቀደም ያሉ ህጎችንና ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ ህጎችንና ደንቦችን በማውጣትና በመተግበር ላይ ትገኛለች። ሕጎችና ደንቦች ለአፈጻጸማቸው መሠረት የሆኑትን አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ የአፈጻጸም ቴክኒካዊ ስልትና መመሪያ ሊዘጋጅላቸው ይገባል። ከእነዚህ ጥረቶች አንዱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን መዘርጋትና በአስገዳጅ ህግ የተደገፈ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በቋሚነት በመላ ሀገሪቱ ማካሄድ ነው።

ኩነቶችን በአግባባዊና ዘመናዊ የምዝገባ ሥርዓት ላይ በመመሥረት የመመዝገብና የማስመዝገብ መብትና ግዴታ እስካልተከበረ ድረስ አንዱ የሰብአዊ መብት ክፍል አልተፈፀመም ማለት ነው። ይኸውም ግለሰቦች ከአግባባዊ የምዝገባ ሥርዓት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻንና የፍችን መከናወን ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እስካልያዙ ድረስ መብታቸውን ማስከበርና ግዴታቸውን መፈፀም አይችሉም።

## 1.2 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የሥነ-ህዝብ መረጃ አቅርቦት

በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት ዘርፍ ሶስት መሠረታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ይታወቃሉ። እነርሱም የቆጠራ መንገድ (Enumeration Method)፣ የምዝገባ

መንገድ (Registration Method) እና የአስተደዳደር መንገድ (Administrative Method) በመባል ተለይተዋል (UN,1955)። በቆጠራ መንገድ የሚካተቱ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ያጠናን ዘዴዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች (Population and Housing Censuses) እና የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናቶች (Demographic Sample Surveys) ሲሆኑ በምዝገባ መንገድ የሚካተቱት ደግሞ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ (Vital Statistics Registration) እና የሕዝብ ምዝገባ (Population Register) ናቸው። ሶስተኛው መንገድ ማለትም የአስተዳደር መንገድ ከአስተዳደር መዛግብት (Administrative Records) የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ያቀፈ ሲሆን በአመዛኙ በደጋፊነት (Supplementary) የሚያገለግሉ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች የሚገኙበት ነው። ስለሆነም በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ዘርፍ ዋነኞቹ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በአፈጣጠራቸው፣ በሚያቀርቡት መረጃ ዓይነትና በአጠቃቀማቸው ልዩነትና አንድነት አላቸው።

በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓትን የማቋቋም አስፈላጊነትን ለመረዳት ለሥርዓቱ ግብዓት የሚሆኑ የኩነቶች መረጃዎች ከሚሰጡት ግልጋሎት አንፃር መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል። ለአንድ ሀገር ፖለቲካዊ አስተዳደር አደረጃጀት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን፣ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት እንዲሁም የእነዚህን ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ለመፈጸምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ በግብዓትነት የሚፈለጉ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች በአግባባዊና ዘመናዊ ሁለት ዋነኛ የመረጃ አሰባሰብ መንገዶች ይሰበሰባሉ። በአንድ ወገን አንድ ወቅትን የተመለከቱ የህዝብ ብዛትና ባህርያትን የሚያመላክቱ መረጃዎች በሕዝብና ቤት ቆጠራና መሰል ናሙና ጥናቶች በቆጠራ መንገድ የሚሰበሰቡ ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ የህዝብ ብዛት ዕድገትን የሚወስኑ የወሳኝ ኩነቶች ብዛት፣ ምጥነትና ባህርያት መረጃዎች በቀጣይነትና በቋሚነት በወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት በምዝገባ መንገድ ይሰበሰባሉ። እነዚህም መረጃዎች በተለይም ከመንግስት አስተዳደር የመረጃ ፍላጎት አንፃር ለህዝባዊ ምርጫ፣ የመንግስትን የበጀት ድልድል ለማድረግ፣ ለትምህርት፣ ለጤናና ተመሳሳይ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ዕቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፀምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ በሀገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ አልፎም በትንሹ አስተዳደር ዕርከን ደረጃ ወቅታዊነታቸውንና አስተማማኝነታቸውን ጠብቀው በቀጣይነትና በቋሚነት ይፈለጋሉ። ለተጠቀሱት ማህበረሰባዊ የተግባር ዘርፎች የሚፈለጉትን መረጃዎች በጥራትና ወቅታዊነታቸውን በመጠበቅ ለማስገኘት የየወቅቱን የህዝብ ብዛት (Stock) እና ቀጣይ ለውጦችን የሚከታተሉ (Flow) የመረጃ አሰባሰብ ስርዓቶችን በማጣመር መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናቀር ይጠይቃል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለቆጠራው ዓመት የሕዝብ ብዛት መረጃን የሚያስገኝ ሲሆን ይኸን መረጃ ወቅታዊ ለማድረግ የየዓመቱን የህዝብ ብዛትና የዕድገት ምጥነትን ለማስላት የሚያስችሉ በዋነኛነት የወሳኝ ኩነቶች (የልደትና የሞት) ብዛትና የኩነቶች ምጣኔ ስታትስቲክስ መረጃዎች ቀጣይና ቋሚ ከሆነ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት መገኘት አለባቸው። በሌላ አገላለጽ በቆጠራዎች መሃከል (Inter Censal) እና ከቆጠራዎች በኋላ (Post Censal) የህዝብ ብዛትና የዕድገት ምጣኔ ስሌትን በወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ በቀጣይነትና በቋሚነት እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የስነ-ህዝብ መረጃዎችን ለማግኘት ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚሰበሰቡ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች መገኘት ይኖርባቸዋል።

ከዚህም በላይ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች የወደፊት የህዝብ ብዛት ትንበያዎችን (Population Projection) በአግባባዊ መንገድ ለማድረግ የሚያስችሉ በዋነኝነት የልደትና የሞት እሳቤዎችን (Assumptions) ለማዘጋጀት ወሳኝ የግብዓት መረጃዎች ናቸው። እንደሚታወቀው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ በቀጣይነትና በቋሚነት በአግባባዊ መንገድ የሚገኘው ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ነው። ሆኖም በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት እስከዛሬ ባለመቋቋሙ የተነሳ ከላይ በአጭሩ የተመለከቱትን የመረጃ ክፍተቶች ከወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ማስገኘት አልተቻለም። ይኸም በመሆኑ ከሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓመት በኋላ በተለይም የልማት ማዕከል በሆኑት በወረዳና ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች የሕዝብ ብዛት፣ ምጥነትና ባህርያት መረጃዎችን ማስገኘት አልተቻለም። ይኸም ሁኔታ በርካታ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎት አሰጣጥ የዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና የአፈጻጸም ግምገማዎችን በአስተማማኝ የስነ-ህዝብ መረጃዎች ላይ በመመሥረት ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መፍጠር እንደማያስችል ግልጽ ነው።

## 2. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ተዛማጅነት ያላቸው ህጎች

### 2.1 የ1952 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ እና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

የ1952 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ከተደነገገ ከ 40 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። በሕጉ አንደኛ መጽሐፍ ስለሰዎች በሚመለከተው ክፍል በምዕራፍ 3 አንቀጽ /47-153/ ባሉት ድንጋጌዎች ሥር የክብር መዝገብ ጽሁፎች አዘገጃጀት ሥርዓት በዝርዝር ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ምዝገባን የሚመለከተው ይኸው ክፍል በሥራ ላይ የሚውልበት ቀን በነጋሪት ጋዜጣ ተወስኖ እስከሚታወጅ ድረስ ተፈፃሚ እንደማይሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3361 ተገድቧል። ሕጉ ምንም እንኳን በወቅቱ ካለው የአስተዳደር ሥርዓት፣ አመለካከት፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ደረጃ ጋር ተገናዝቦ የተዘጋጀ ነበር ቢባልም በዚያ መልኩም እንኳ ተግባራዊ ሳይሆን ቆይቷል።

በፍትሐብሔር ህጉ ስለክብር መዝገብ ጽሁፎች አዘገጃጀት የተመለከቱት አንቀጾች የምዝገባውን አስፈላጊነት፣ ይዘትና አፈጻጸም ለእያንዳንዱ ዜጋ ሕጋዊ መብቱን ከማስከበር መርህ አንጻር የተደነገጉ ባለመሆናቸው በወቅቱ ከነበረው ዓለም አቀፍ ግንዛቤ ጋር የሚራመዱ አልነበሩም። ከዚህም በላይ የኩነቶች ምዝገባ ለሕብረተሰቡ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት፣ አፈጻጸማቸውን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችሉ የስነ-ህዝብ መረጃዎች መመዝገብ እንዳለባቸው አላካተተም። ሕጉ እነዚህን መሠረታዊ የኩነቶች ምዝገባ መርሆዎችን ካለማካተቱም በላይ የኩነቶች ጽንሰ-ሀሳብና ትርጉም የጠበበ፣ ወቅታዊነትና ቀጣይነት ያለው መረጃ ለመዘርጋት የሚያስችል አሰራር የሚፈጥር አልነበረም። በአጠቃላይ ሕጉ በመጠኑም ቢሆን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አካል የሆኑ አሠራሮችን የጠቀሰ ቢሆንም አሁን ሀገሪቱ ካለችበት የሕብረተሰብ የዕድገት ደረጃ፣ በዋነኝነትም ከህገ-መንግስቱ ጋር እንዲጣጣምና ዓለም አቀፍ መርሆዎችን በተከተለ መልኩ እንዲሻሻል መደረጉ የግድ ነው።

## 2.2 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥትና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

በ1987 ዓ.ም ጸድቆ በሥራ ላይ የዋለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት በርካታ የሰው ልጆች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን ከማካተቱም በላይ እነዚህም ህገ-መንግስታዊ ዕውቅና የተሰጣቸው መብቶችና ነፃነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶችና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲተረጎሙ ያዛል። በርካታ ታዳጊ ሀገሮች የሲቪል፣ የፖለቲካና የማህበራዊ መብቶችን በህገ-መንግሥትና መሰል መሪ ህጎች ማሳወቁ በተለመደው መንገድ በመከናወን ላይ የሚገኝ ቢሆንም ቅሉ ለመብቶቹ መተግበር ወይም መጠበቅ መሣሪያ የሆኑትን የማስፈፀሚያ መብቶችን እውቅና በመስጠቱም ሆነ በመተግበሩ ረገድ ብዙም እንዳልተገፋበት በተለይም የአፍሪካ ሀገራት ተሞክሮ በግልጽ ያሳያል። መሠረታዊ የሲቪል፣ የፖለቲካና የማህበራዊ መብቶች ማስፈፀሚያ ወይም መጠበቂያ መብቶች ባልተዘረጉበት/ ባልተተገበሩበት ሀገር የዜግነትና ሌሎች መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን በአግባቡና በህጋዊ መንገድ፣ በቀጣይነት፣ ለዘለቄታውና ወቅታዊ ምላሽን መስጠት በሚያስችል የህዝብ አስተዳደር አሰራር መደገፍ አይቻልም።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 36(1) (ለ) - ማንኛውም ህፃን ስምና ዜግነት የማግኘት መብት እንዳለው በሚገልፀው አንቀፅ መሠረት ህፃናቱን የመብቱ ተጠቃሚ ለማድረግ መንግሥት በቀዳሚነት በሀገሪቱ የልደት ምዝገባ ለመዘርጋት የሚያስችለውን የኩነቶች ምዝገባ ህግ መደንገግና የምዝገባ ሥርዓቱን መዘርጋት እንደሚጠበቅበት ይታወቃል። በተመሳሳይ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ (6/1) "ወላጆቹ/ ወላጆቿ ወይም ከወላጆቹ/ ከወላጆቿ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ ነው/ናት" በማለት በኢትዮጵያ የዜግነት አሰጣጥ ሥርዓት በትወልድ ሀረግ ላይ እንደሚመሠረት የተደነገገውን ህጋዊ ሥርዓትን ተከትሎ ለመተግበር ከዜግነት ህግ በተጨማሪ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በሀገሪቱ መዘርጋትን እንደሚጠይቅ ይታወቃል። በሌላ አገላለጽ በኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት መሠረት ለህፃናትም ሆነ ለአዋቂዎች ዜግነትን ለመለየት መነሻው የወላጆች ዜግነት ነው፣ ለዚህም ሁሉን አቀፍ የልደት ምዝገባ ሥርዓትን በተፋጠነ መንገድ የመዘርጋትን አስፈላጊነት ያመለክታል።

በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 36(ሐ) ላይ ህፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና በወላጆቻቸው የመጠበቅ መብት እንደተሰጣቸው የሚገልጽ የህግ ዕውቅና ተደንግጓል። ስለ ህፃናት ስም የማግኘት፣ ወላጆቻቸውን የማወቅና በወላጆቻቸው የመጠበቅ መብት ስናነሳ ለነዚህ መብቶች መከበር መሠረቱ የልደት መመዝገብ መብት መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። በተመሳሳይ ሁኔታ የዜግነት መብት አፈፃፀም አስተዳደራዊ ሥርዓት አዘረጋግ መነሻው የልደት መመዝገብ መብት ተግባራዊ መሆን ነው። በርግጥ ከዚህም በላይ የወላጆች ዜግነት ለህፃናቱ ዜግነት ውሳኔ አሰጣጥ መሠረት ስለሆነ የወላጆች ህጋዊ የልደት መዝገብ መረጃ መኖር በኢትዮጵያ በዜግነት ሰነድ ዝግጅት ሒደት ውስጥ ወሳኝ ነው።

በተለያዩ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ላይ እንደተገለጸው ሁሉ በኢትዮጵያ ህገ-መንግስትም ህፃናት ከልጅነት ጋብቻ መጠበቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል። በርግጥ ይህ ድንጋጌ

በቤተሰብ ህጉ ትንሹን የጋብቻ ዕድሜ የህግ ዕውቅና በመስጠት መብቱ እንዲጠበቅ የሚያደርግ አንቀጽ አካቷል። ይሁን እንጂ እንደሌሎች መብቶች ሁሉ የመብቱ ባለቤት የሆኑት ህፃናት ራሳቸውን ከልጅነት ጋብቻ ለመጠበቅ የሚያስችላቸው ህጋዊ መረጃ እንዲኖራቸው የሚያደርግና፣ መንግሥትም የነዚህ ህፃናት መብት እንዳይደፈር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያበቃውን አግባባዊ የአስተዳደር ሥርዓት መሠረት መጣል ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የህፃናቱ ቤተሰብም ሆነ ማህበረሰቡ ህፃናት በህግ በተደነገገላቸው የጋብቻ ዕድሜ ላይ ሳይደርሱ ለማግባት እንዳይገደዱ የሚጠብቃቸውንና መንግሥትም ይህንኑ ለማረጋገጥ እንደመረጃ የሚገለገልበትን የልደት የምዝገባ ሰነድ ማለትም ህፃናቱ በተወለዱ ጊዜ ተመዝግቦ የተያዘ ዝርዝርና ህጋዊ የልደት መዝገብ እንዲኖር አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በህገ-መንግስቱ ለአፈፃፀማቸው የኩነቶች መመዝገብ መብት መከበርን የግድ የሚሉ በርካታ አንቀፆች ተካተዋል። ለምሳሌ በአንቀጽ (36/3) "ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ... ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው" የሚለው ድንጋጌ፣ በአንቀጽ /34(1)/ "በህግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች . . . በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፤ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፤" እንዲሁም የዲሞክራሲ መብት ከሚገለጽባቸው አንዱ የሆነው በአንቀጽ (38) የተደነገገው የመምረጥና የመመረጥ መብቶችን ወደ ተግባር ለማምጣትና ተገቢውን ፍትህ መስጠትና የመብት ተጠቃሚ ለማድረግ የኩነቶች መመዝገብ መብትን የሚያስከብር የኩነቶች ምዝገባ ህግና ሥርዓትን ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በሚያካትት መልኩ በመንግሥት ተግባራዊ መደረግን የሚጠይቁ ናቸው።

እንደተተቀሩት በርካታ ታዳጊ ሀገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም ይኸን አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል መሠረት ማለትም የዜግነትና የሰብዓዊ መብት ማስጠበቂያ መብቶች (የወሳኝ ኩነቶች መመዝገብ መብት) በህግ እውቅና የሚያገኙበት የህግ ዘርፎች ገና ተግባራዊ አልሆኑም። በሌላም በኩል የሰብዓዊ መብት ማስፈጸሚያ/ ማስጠበቂያ መብቶች ተግባራዊ የሚሆኑበት የአሰራር ስልትና ሥርዓት ማለትም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግና ሥርዓት አልተቋቋሙም። በመሆኑም በህግ ያልተደገፈ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባልተዘረጋባቸው ሀገሮች የዜግነትና መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን በአግባቡና ለዘለቄታው ሊተገበሩና ሊከበሩ በሚችሉበት አኳኋን በሥራ ላይ መዋል አዳጋች ነው።

## 2.3 የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

የቤተሰብ ሕግ "ቤተሰብ የህብረተሰብ የተፈጥሮ መነሻ" መሆኑን ከሚደነግገው የህገ-መንግሥት መርህ ላይ በመመሥረት የቤተሰብ ጥበቃን፣ በተጋቢዎች ሙሉ ፈቃድና ነፃነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ የሚፈፀምበትን፣ የሕፃናት መብትን፣ የሴቶች መብትን... ወዘተ. ለማስፈፀም የሚዘጋጅ የህግ ዘርፍ ነው። ከ1952 ዓ.ም. ፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ስለቤተሰብ የተደነገገውን በማሻሻል በ1992 ዓ.ም የጸደቀው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አፈፃፀሙ በሀገሪቱ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት ላይ የተመሠረተ መሆኑን የህግ አንቀጾቹ ይገልፃሉ። ይኸንኑ በመገንዘብ በህጉ አንቀጽ 321(1) የፌደራሉ መንግሥት ህጉ በሥራ ላይ በዋለ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕጉ

ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው መስተዳድሮች የሚያገለግል የምዝገባ ህግ እንዲያወጣና አስፈላጊ ተቋሞችንም እንዲያደራጅ ደንግጓል።

## 3. በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ

### 3.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ አዘገጃጀት መርህ

በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ አዘገጃጀትና አተገባበር በህገ-መንግስቱ ከተቀመጠው የፌደራልና የክልል መንግሥታት ህግ የማውጣት የስልጣን ክፍፍል መርህ አንፃር ምን ዓይነት አሠራር ሊከተል እንዲገባው አስቀድሞ መወሰን ይገባዋል። በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ተለይቶ የተቀመጠ ጉዳይ አይደለም። ሆኖም የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በርካታ የፍትሀብሄር ጉዳዮችን ለማስፈጸም ካለው ቁርኝትና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ባለው ልምድ የኩነቶች ምዝገባ ህግ የፍትሀብሄር ህጉ አካል ተደርጎ እየተወሰደ ሲሰራበት የነበረ ከመሆኑ አንፃር በህገ-መንግስቱ ተለይቶ ያለመቀመጡ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ከሚያስገኘው ህጋዊ የማንነት መረጃዎች በተለይም ዜግነትንና መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ካላቸው ቁልፍ ሚና እንዲሁም ከምዝገባው የሚገኙት የስነ-ሕዝብ መረጃዎች ከትንሹ የመስተዳድር እርከን ጀምሮ እስከ ሀገር አቀፍ ደረጃ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ዕቅድና ፖሊሲዎችን የማዘጋጀትና ለፖለቲካ ሥርዓቱ ዝግጅትና አፈጻጸም ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር የህግ አቀራረጽ ሥርዓቱ ሰፋ ተደርጎ ሊታይ ይገባል። ከዚህ አንፃር በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55(6) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት "አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር ሲባል በፌደራል መንግሥት ሕግ እንዲወጣላቸው የሚያስገድዱ ለመሆናቸው በፌደሬሽን ምክር ቤት የታመነባቸው የፍትሀብሄር ህጎችን" እንደሚያወጣ ደንግጓል።

በአንድ አገር ወይም የአስተዳደር ክልል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ለማቋቋም ሲታሰብ በቅድሚያ መዘጋጀት ያለበት የአገሪቱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዕድገት ደረጃ የሚመጥን፣ የሕዝቡን ባህል፣ ሃይማኖትና አኗኗር እንዲሁም ዓለም አቀፍ መርሆዎችን ያገናዘበ የምዝገባ ሕግ (Civil Registration Law) ነው። የሕጉ መኖርና መተግበር ግለሰቦች፣ ማህበረሰቡ፣ መንግሥትና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት መብቶቻቸውን፣ ኃላፊነታቸውንና ግዴታዎቻቸውን አውቀው ህጋዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትን ዘመናዊና አግባባዊ የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት ለመፍጠር የሚያስችሉ ወሳኝ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል። ይህም የምዝገባ ህግ ከአገሪቱ ሕገ-መንግሥት፣ ከተለያዩ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችና ስምምነቶች ጋር የማይጋጭና የማይቃረን መሆን ይኖርበታል።

የምዝገባ ሕጉ የምዝገባው ዓለም አቀፋዊ የቴክኒክ ምሪት እና አስተዳደራዊ አወቃቀር መሠረቶችን በመንተራስ እንዲሁም የሀገሩን የመንግሥት የህግና የአስተዳደር አወቃቀርና የአስፈፃሚ ተቋማትን አደረጃጀት በማገናዘብ በሚዘጋጀው ቴክኒካዊ ጥናት ላይ ተመሥርቶ ሊቀረጽ ይገባል። ለምዝገባው አፈፃፀም የሕጉ አስገዳጅነት፣ የአስፈጻሚ ተቋማቱ ቋሚነትና የአሠራሩ ዘላቂነት ዋና መሠረቶች ናቸው። የምዝገባ ሕጉ መኖር ግለሰቦች፣ ሕብረተሰቡ፣

መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን አውቀው የኩነቶች ምዝገባን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያስችላል። ሕጉ የምዝገባ አሠራር መመሪያና ማስፈፀሚያ ደንብ በመሆን የምዝገባው ሥርዓት እያደገ፣ እየተሻሻለና በዘመናዊ አሠራር እየተጠናከረ እንዲሄድ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ መቀረጽ ይገባዋል።

የምዝገባውን ሥርዓት ለማቋቋም የሚቀረፀው ሕግ የምዝገባውን የተለያዩ የአመዘጋገብ አሠራሮችን፣ የአስፈጻሚ ድርጅቶች አስተዳደራዊ መዋቅርን፣ የምዝገባውን የአፈጻጸም መመሪያ አተገባበር፣ ... ወዘተ ግልጽ በሆነ መንገድ ማብራራትና መተርጎም ይኖርበታል። ሕጉ በአገሪቱ ያለውን የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ሥርዓት አወቃቀርና አስተዳደር እንዲሁም ከምዝገባው ጋር የሚኖረውን ቁርኝት ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

## 3.2 በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ይዘት

የኩነቶች ምዝገባ የህግ አቀራረጽ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የሚቀረጸው የምዝገባ ህግ የሚከተሉትን ዓበይት ጉዳዮች ያካተተ ሊሆን ይገባል።

1. የሕጉ መደንገግ ያስፈለገበት ምክንያትና ዓላማ መግለጫ፣
2. የሚመዘገቡ የወሳኝ ኩነቶች ዓይነትና ትርጉም፣
3. የወሳኝ ኩነቶችን መከሰት ማስታወቅ፣ ማስመዝገብና መመዝገብ ግዴታ ስለመሆኑ፣
4. የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ የጊዜ ገደብ፣
5. በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ አለመመዝገብ/ አለማስመዝገብ የሚያስከትለውን ጉዳትና ቅጣት፣
6. የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ቅጾች አመዘጋገብ፣ አያያዝና አስተላለፍ፣
7. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ አጠናቃቀርና አጠቃቀም፣
8. የምዝገባው ሥራ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ መዋቅር፣ የተቋማት ተግባርና ሀላፊነት፣
9. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሹም ተግባርና ሀላፊነት፣
10. የጠቋሚ፣ የአስመዝጋቢና የመዝጋቢ ኃላፊነትና ተግባር፣
11. የምዝገባው ሥራ አፈጻጸምና አደረጃጀት፣
12. የምዝገባ ዶኩመንቶች፣ መዝገቦችና ምስክር ወረቀቶች ቅርጽና ይዘት፣
13. የምዝገባ ዶክመንቶች አጠቃቀም ሥርዓት፣
14. የምዝገባ ዶኩሜንቶች አያያዝ፣ አቀማመጥና አስተላለፍ፣
15. በምዝገባው ሥራ የተሠማሩ ተባባሪ አካላት ኃላፊነትና ተግባር፣
16. የምዝገባው ሥራ በጀት ምንጭና አወጣጥ ሥርዓት፣
17. ስለ ምዝገባው ተከታታይነት፣ ቋሚነትና አገር አቀፍ ይዘት እንዲሁም አስገዳጅነት፣ . . . ወዘተ

# 4. በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት

## 4.1 በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት መርህ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባዘጋጃቸው ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ መመሪያዎች በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አወቃቀር ሁለት መሠረታዊ አደረጃጀቶችን በግልጽ በመለየት መዋቀር እንደሚገባው ይገልፃል። እነርሱም የምዝገባ ሥርዓቱን "ድርጅታዊ" እና "አስተዳደራዊ" አወቃቀር ይመለከታሉ። በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ "ድርጅታዊ" አወቃቀር ሁለት መልክ ሊኖረው ይችላል። ይኸውም "የተማከለ" ወይም "ያልተማከለ" አደረጃጀት በመከተል ሊዋቀር ይችላል። በሌላም በኩል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ "አስተዳደራዊ" አወቃቀር የተለያየ መልክ ይዞ ሊደራጅ ቢችልም በዋንኝነት ተለይተው የሚታወቁት አስተዳደራዊ አደረጃጀቶች ራሱን ችሎ የሚተዳደር የምዝገባ ሥርዓት እና ራሱን ችሎ የማይተዳደር (በሌላ ተቋም ሥር የሚተዳደር) የምዝገባ ሥርዓት በመባል ይታወቃሉ።

ከዚህ አንፃር የአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር የሀገሪቱን ሥርዓተ-መንግስት አደረጃጀትና የመንግስት ተቋማትን አስተዳደራዊ አወቃቀር መሠረት ባደረገ ጥናት ላይ በመመሥረት ሊደራጅ ይገባል። በአንድ ሀገር የምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ አወቃቀር የተማከለ ወይም ያልተማከለ መሆኑን ለመወሰን አስቀድሞ ሙያው በሚመለከተው/ታቸው ተቋም/ማት ጥልቅ ጥናት ማድረግን ይጠይቃል። በዚህ መስክ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በተከታታይ ባደረጋቸው የግምገማ ጥናቶች መሠረት በዋንኝነት ሀገሪቱ ከምትከተለው የፌደራል ሥርዓተ-መንግስት አስተዳደር፣ ከአገሪቱዋ የቆዳ ስፋትና ከሕዝብዋ ቁጥር ከፍተኛነት አንፃር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓቱ ድርጅታዊ አወቃቀር "ያልተማከለ" ሊሆን እንደሚገባ ጽ/ቤቱ ያምናል። ይኸም ማለት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባርን የማከናወንና የማስፈፀሙ ሥራና ኃላፊነት የክልል መስተዳድር መንግሥታት መሆን እንደሚገባው ያመለክታል። ይህም ሆኖ በየክልል መስተዳድሩ የሚከናወነውን የምዝገባ ሥራ የቴክኒክ ብቃት የሚከታተልና የሚገመግም እንዲሁም ተመሳሳይነት ያላቸው ግለሰባዊ የህግና የስነ-ህዝብ መረጃዎች የሚዘጋጁበትን አሠራር የሚያደራጅ ሀገር አቀፍ መንግስታዊ ተቋም መኖር ይኖርበታል። እንደሚታወቀው በአንድ ሀገር የምዝገባ ሥራ ያልተማከለ በሚሆንበት ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን ሥራ የሚያስተባብርና ሀገራዊ ይዘቱን የሚከታተል ሀገራዊ የቴክኒክ ተቋም መኖሩ ግድ ነው። እንዲህ ባለ "ባልተማከለ" የምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋመው ተቋም ተግባርና ሀላፊነት በዋንኝነት የምዝገባውን ቴክኒካዊ አሰራር በማስተባበር ሥራ ላይ የሚገደብ ስለሚሆን ተቋሙ የሀገሪቱን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ የሚያጠናቅርና የሚያሰራጭ እንዲሁም የሀገሪቱ የምዝገባ ማዕከላዊ መዝገብ ቤት ሆኖ የሚያገለግል ቢሆን ይመረጣል።

በተመሳሳይ የአንድ አገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አስተዳደራዊ አወቃቀር/አደረጃጀት ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚገባ ለመወሰን ዋነኛውና ወሳኙ ጉዳይ የሀገሪቱ ተጨባጭ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የዕድገት ደረጃና የሕዝብ አስተዳደር ተቋማዊ አወቃቀር ነው። ይኸም ሆኖ የኩነቶች

ምዝገባ ተግባር መከናወን የሚገባው ለሕብረተሰቡ ቅርብ በሆነው በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን መሆን እንደሚገባው የምዝገባ ሥርዓቱ ዓለም አቀፍ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አሠራር መርህ ያዛል። እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የህዝብ አስተዳደር መዋቅራዊ አደረጃጀት ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የቀበሌ መስተዳድር ነው። የቀበሌ መስተዳድር የዕዝ ሰንሰለትም እስከ ክልል መስተዳድር የሚደርስበት ሥርዓት ተዘርግቶ ይገኛል። በመሆኑም በኢትዮጵያ የምዝገባ ሥርዓቱ አስተዳደራዊ አወቃቀርና አደረጃጀት የነባር ተቋማትን አወቃቀር በየአስተዳደር ዕርከኑ ተከትሎ የሚደራጅ ሊሆን እንደሚገባ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እምነት ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር አወቃቀር የወሳኝ ኩነት ምዝገባውን በመፈፀም ከቀበሌ መስተዳድር የተሻላ ተቋም ሊኖር ይችላል የሚል ግምት የለም። በመሆኑም የኩነቶች አመዘጋገብ ሥርዓት በምዝገባ ህጉ በሚገለፀው መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ሥር ማደራጀት ይፈልጋል። በተጨማሪም እንደ ቀበሌው ስፋትና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ንዑስ የምዝገባ ጣቢያዎች በቀበሌው ሥር ሊቋቋሙ ይችላሉ።

ከላይ በኢትዮጵያ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት ያልተማከለ ቢሆን እንደሚመረጥ የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው አስተዳደራዊ አወቃቀር የክልል አስተዳደር መንግስታትን የተቋማት አስተዳደራዊ አወቃቀር የሚከተል ሊሆን እንደሚገባ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እምነት ነው። በዚህ ረገድ በየክልል መስተዳድሩ የምዝገባ ሥርዓቱ አስተዳደራዊ አወቃቀር በክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመሥረት ክልሎች በሚሰጡት አስተያየት ላይ የሚመሰረት ቢሆንም በክልል እና በተዋረድ የመስተዳድር እርከኖች የሚቋቋሙ የምዝገባ ጽ/ቤቶች መዋቅራቸው እስከ ቀበሌ መስተዳድር የተዘረጋና ከቀበሌ መስተዳድሮች ጋር ቀጥታ የትዕዛዝና የማስፈጸም ግንኙነት ያላቸው ሊሆኑ እንደሚገባ መገንዘብ ይገባል። ይኸም ሲሆን እንደኮሚሽኑ ጽ/ቤት የግምገማ ጥናት በክልልም ሆነ በዞን (አስፈላጊነቱ ከታመነ) እና በወረዳ ደረጃ የሚቋቋሙ የምዝገባ ጽ/ቤቶች የነባር ተቋማትን መዋቅር የሚከተሉና የምዝገባ ሹሞችም በየደረጃው ካሉ የሥራ አስፈፃሚ አባላት ለምዝገባው ሥራ ካላቸው የሀላፊነት ድርሻ ጋር እየተገናዘበ በክልሉ ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሚሾሙ እንደሚሆኑ ነው።

## 4.2 በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት መርህ

እንደተባበሩት መንግሥታት አመለካከትና በአብዛኛው ሀገራት ተሞክሮ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት "የተማከለ" ነው። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 103 ን መሰረት በማድረግ የተቋቋመው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን፣ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ኮሚሽኑ የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥር በየጊዜው እንደሚያጠናና ቆጠራ እንደሚያካሂድ ደንግጓል። ይኸ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ የሚያመለክተው ኮሚሽኑ ሁለት ዋና ዋና ተግባራትን እንደሚያከናውን ነው። አንደኛው የህዝብ "ቆጠራ" ን ማካሄድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የህዝቡን ቁጥር በየጊዜው "ማጥናት" ነው።

በመሰረቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ለፖለቲካ ሥርዓቱ አደረጃጀትም ሆነ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ዕቅድ ዝግጅት፣ ዕቅድ አፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር

ተግባር ለማዋል በዋንኛነት በሁለት የስነ-ህዝብ መረጃ መሰብሰቢያ አሰራሮች/ሥርዓቶች መደገፍ ይኖርበታል። ይኸንኑ ሁኔታ በመገንዘብ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 4(2) ኮሚሽኑ የሕዝብ እና የቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሰራበት መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ እንደሚገባው ተደንግጓል። ይኸ የኮሚሽኑ ሁለተኛ ዓላማ በዘርፉ የሀገሪቱን የረጅም ጊዜ ዓላማ ያመላከተና ቋሚና ቀጣይነት ያለው የሥነ-ህዝብ መረጃ ሥርዓት እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ለመፍጠር የሚያስችል ተግባርን የሚመለከት ነው። የዚህ ዓላማ የተግባር መነሻው በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ወደ ሕዝብ ምዝገባ ማሸጋገር ነው። የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ አግባባዊው የመረጃ ምንጭ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ነው። ይኸው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታ በተለይም በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 7(3፣ 6፣ 7 እና 8) የተገለጹትን የመረጃ ፍላጎቶች ወቅታቸውን በጠበቀና በጥራቱ የተሟላ መረጃ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ማስገኘት አይቻልም።

በአንድ አገር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የተማከለ ወይም በአንድ ማዕከል ቁጥጥር ሥር ሲሆን ጽንሰ ሃሣቦች፣ ትርጓሜዎችና፣ የሚዘጋጀው የስነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ ተመሣሣይና ተነፃፃሪ እንዲሆን ያስችላል። ከሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደምንግረው በአብዛኛው አገሮች የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ አደረጃጀት የተማከለ ነው።

# ክፍል-2 በቀረበው የህግ ረቂቅ ላይ አጠቃላይና በየአንቀጹ ላይ የቀረበ አስተያየት

## 5. አጠቃላይ

በፍትህና ህግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በሚያዝያ ወር 1993 ዓ.ም ተዘጋጅቶ "ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ለማቋቋምና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ረቂቅ" በሚል ርዕስ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው የህግ ረቂቅ ምንም እንኳ ለመነሻነት ጠቀሜታው የጎላ ቢሆንም በሙያና የሥራ ባህርያቸው በባለቤትነት ጭምር አዋጁን በማርቀቅ ሂደት ተሳታፊ ሊሆኑ የሚገቡ መሥሪያ ቤቶችን ባሳተፈ መልኩ ረቂቁ ባለመዘጋጀቱ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ካለማካተቱም በላይ ዘርፉ የደረሰበትን የእድገት ደረጃ ማገናዘብ ይቀረዋል። በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ የሚገቡ አጠቃላይ የሆኑ ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መርህ በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ረቂቅ ዝግጅት በዋንኝነት የህግ፣ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስና የጤና ተቋማትን ባቀፈ አብይ የቴክኒክ ኮሚቴ አማካይነት መረቀቅ እንደሚገባው ይገልፃል። ከዚህም በላይ ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኘውን መረጃ በመጠቀም ግንባር ቀደም ተቋማትን ለምሳሌ እንደ ህዝባዊ ምርጫ አስፈጻሚዎችን፣ የመታወቂያ ግል.ጋሎት ሰጪ አካላትን፣ የዜግነትና ኢሚግሬሽን ጉዳዮች አስፈጻሚ ተቋማትን፣ የመብት ተከራካሪ ተቋማትን (ለምሳሌ የሴቶችና ህጻናት መብት፣...)፣ አግባብ ያላቸው የሙያ ማህበራትን፣ . . . ወዘተ የመረጃ ፍላጎት በተከተለና በተደራጀ አመራር ረቂቁ መዘጋጀት ይገባው ነበር፤

ለ) በ1952ቱ ፍትሀብሄር ህግ ላይ እንደታየው ጉድለት ሁሉ በዚህኛውም ረቂቅ ከኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚገኘው የስነ-ህዝብ መረጃ አሰባሰብ፣ መረጃ የማስተላለፍ መዋቅራዊ አደረጃጀት ሥርዓት በህጉ መካተት ሲገባው ጭራሹንም አለመጠቀሱ፤

ሐ) የምዝገባ ሥርዓቱ ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎቶች በጥምረት እንዲያስገኝ የሚያስችለውን የኩነቶች ጽንሰ-ሀሳብና ትርጓሜ በዘርፉ ዓለም አቀፍ የመረጃ አሰባሰብ መርሆዎችን ተከትሎ ያለመቀረጹ፤

መ) የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በሀገሪቱ ህገ-መንግስታዊ የመንግሥት አወቃቀር ላይ በመመሥረት በተደረገ ጥናት ላይ ተመሥርቶ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀሩ መወሰን ሲገባው፣ ያለምንም መሰረት በፍትሀብሄር ህጉ የነበረውን የምዝገባ አደረጃጀት በመከተል መቅረቡ ትክክል ያለመሆኑ፤

ሠ) በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት በዋንኝነት ማካተት ከሚገባቸው ኩነቶች ፍቺ አንዱ ነው። በዚህ ረገድ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፍቺና ጋብቻ ሳይነጣጠሉ በምዝገባ ሥርዓቱ መካተት እንደሚገባቸው በዘርፉ ባዘጋጃቸው መመሪያዎች ላይ አስቀምጧል። የቀረበው ረቂቅ የፍትሀብሄር ህጉን በመከተል

ያለምንም የጥናት መሰረት ፍቺን በተጨማሪ መግለጫ (Complemantary Notation) እንዲያዝ ማድረጉ ትክክል ያለመሆኑ፤

ረ) ከዋነኛ ወሳኝ ኩነቶች በተጨማሪነት በመግለጫ (Complemantary Notation) የሚመዘገቡ (ለምሳሌ ጉዲፈቻ፣ ጋብቻ እንዲፈርስ መቋረጥ፣ . . . ) ኩነቶችን ዓለም አቀፍ መርህን ተከትለው እንዲካተቱ በሚያደርግ አኳኋን በረቂቁ አለመቀመጣቸው፤

ሰ) የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚያስገኘው አንዱና ዋነኛው ጥቅም ለግለሰቦች የሚያስገኘው ህጋዊ የማንነት መረጃ ነው። ይኸም መረጃ የኩነቶች ምስክር ወረቀት በመባል ይታወቃል። ሆኖም በቀረበው ረቂቅ ህግ ስለ ምስክር ወረቀት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ምንም የተገለጸ የአዘገጃጀትም ሆነ የመረጃ አሰጣጥ የህግ ጉዳይ ያለመኖር፤

ሸ) በፍትሀ-ብሄር ህጉ ከአንቀጽ 1-47 ያሉት አንቀጾች አሁን ከሚታሰበው የምዝገባ ህግና አሰራር አንጻር መሻሻል የሚገባቸው ስለሚሆን አግባብ ባለው ህግ ተሻሽለው የሚቀርቡበት አሰራር ቢዘጋጅ፤

የሚሉት በዋነኝነት የሚጠቀሱና በረቂቁ ላይ የታዩ መሰረታዊ ጉድለቶች ናቸው። ይኸም በመሆኑ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በኩል በረቂቁ ላይ የቀረቡት የማሻሻያ ሀሳቦች ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለማሙዋላት ይረዳሉ የሚል እምነት ቢኖርም በቀጣይ የማሻሻል ተግባሩን በማከናወን ረቂቁን በማዘጋጀት ሊቋቋም ይገባው የነበረው አብይ የቴክኒክ ኮሚቴ በረቂቁ ላይ ማሻሻያዎችን በማካተት ትልቅ ጠቀሜታ ስላለው የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ጉዳዩን በቅርበት እንዲመለከቱት ጽ/ቤቱ በዚህ አጋጣሚ ያሳስባል።

## 6. በመግቢያው ላይ የተሰጠ አስተያየት

ሀ) የፍቺ ኩነት በምዝገባ ህጉ መካተት የሚገባው በመሆኑ መግቢያው ፍቺን ባካተተ መልኩ ቢዘጋጅ፤

ለ) ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚገኙ ህጋዊ የኩነቶች መረጃ አንዱና መሰረታዊ ጥቅማቸው መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን ለማስጠበቅና አፈጻጸማቸውን ለመከታተል የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት ለመፍጠርና በዚያም ላይ ተመሥርቶ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ለማገዝ መሆኑ ጎላ ባለና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ቢገለጽ፤

ሐ) ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚጠናቀሩት የስነ-ህዝብ መረጃዎች ከሌላ የመረጃ ምንጭ የማይገኙ በተለይም በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን (በቀበሌ መስተዳድር ደረጃ) ለማህበራዊና የኢኮኖሚ ግልጋሎት አሰጣጥና የአፈጻጸም ግምገማ ለማድረግ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን በቀጣይነት የሚያስገኙ መሆናቸው በመግቢያው የመጨረሻ ፓራግራፍ በጎላ መልኩ ቢገለጽ፤

## 7. ምዕራፍ አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌዎች

- በአንቀጽ 1 የተመለከተውን የአዋጁን መጠሪያ አስመልክቶ በአዋጁ ማብራሪያ ላይ የአስያየሙ መነሻ ምዝገባው ከማዕከል ጀምሮ የተደራጀ መሆኑን ለመግለጽና ማዕከላዊ ጽ/ቤት መቋቋሙን ለማመልከት እንደሆነ ያመለክታል። በዚህ አገላለጽና በረቂቅ አዋጁ ማብራሪያ ስለምዝገባ ሥርዓቱ አደረጃጀት እንደተመለከተው በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የምዝገባ ሥርዓት የተማከለ አደረጃጀት እንደሚከተል ያመላክታል። ቀደም ሲል በክፍል አንድ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት ያልተማከለ ሊሆን እንደሚገባ ለመግለጽ እንደሞከርነውና በተለይም ሀገሪቱ ከምትከተው ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓት አንጻር በዋነኝነት የምዝገባ ተግባሩ በቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን የሚፈጸምን ተግባር በማዕከል የአስተዳደርና የኦፕሬሽን ሥራውን ለማቀድ መሞከር የሚመረጥና ተገቢ አካሄድ እንዳልሆነ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በአጽዕኖት ይገልጻል። በመሆኑም ይኸ አንቀጽ መሰረታዊ የጽንሰ-ሀሳብና የቴክኒክ ችግር ያለበት ስለሆነ የምዝገባ ሥርዓቱ ከሚከተለው አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር ጋር ተገናዝቦ ስያሜው እንዲሰጠው ቢደረግ፤
- በአንቀጽ 2 በትርጓሜው ሥር መካተት የሚገባቸው በዋነኝነት የእያንዳንዱ ኩነት ትርጓሜ ዓለም አቀፍ መርሆዎችን በተከተለ አሰራር በጥንቃቄ መቀረጽ ይገባቸው ነበር። ለምሳሌ በፍትሀብሄር ህጉ ለልደት፣ ጋብቻና ሞት የተሰጡት ትርጓሜዎች የምዝገባ ሥርዓቱ እንዲሰጥ ከሚገባው የሰብዓዊ መብት ማስጠበቅ፣ የህግ፣ የአስተዳደርና የስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎቶች አንጻር የተቀረጸ አልነበረም። እነዚህ ወሳኝ ኩነቶች በተለያዩ ሙያዎችና በተባበሩት መንግስታት ልዩ ልዩ ድርጅቶች የተሰጡዋቸው ትርጓሜዎች ስላሉ፣ ይኸንኑ ያገናዘበና ከሀገሪቱ ተጨባጭ የእድገት ደረጃ ጋር በተጣጣመ መልኩ ቢቀረጽ፤
- በአንቀጽ 2 በትርጓሜው ሥር በተጨማሪ መግለጫ (Complemantary Notation) የሚመዘገቡ ኩነቶችን በማካተት ለነዚህ ኩነቶችም ትርጓሜ ቢሰጥ፤
- በአንቀጽ 2 ሥር ትርጉም የሚያሻቸው ጽንሰ ሃሳቦች ለምሳሌ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት፣ ወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት፣ ክብር መዝገብ፣ ክብር መዝገብ ሹም፣ . . . ወዘተ የመሳሰሉት ቢካተቱ የህጉን ግልጽነት ይጨምራል።

## 8. ምዕራፍ ሁለት - ስለምዝገባ ጽሕፈት ቤቶች መቋቋም

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚያስገኛቸው መረጃዎች የግለሰብን ማንነት የሚያስረዱ ህጋዊ መረጃዎች ብቻ ሳይሆኑ ተጠናቅረው ከትንሹ አስተዳደር ዕርከን ጀምሮ እስከ ሀገር አቀፍና ሀገሪቱን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ የስነ-ህዝብ መረጃዎች ምንጭ ነው። ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙ ህጋዊ የግለሰብ መረጃዎች በተለይ በግለሰቦች ዕለታዊ ህይወት ከልደት እስከ ዕልፈት የሚኖራቸው ፋይዳ በርካታ ነው። እነዚሁ ግለሰባዊ መረጃዎች መንግሥት የእያንዳንዱን የሀገሪቱን ዜጋ ማንነት ለማወቅና በማናቸውም የአስተዳደር ዕርከን ደረጃና የማህበረሰብ ክፍል

የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ አገልግሎት አሰጣጥና የልማት ሥራዎች የዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸሙን ለመከታተል አስፈላጊ መረጃዎች ናቸው።

የኩነቶች ምዝገባ የመረጃዎች አመዘጋገብ፣ አጠንቃቀርና መረጃ አሰጣጥ ሥርዓት ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከግለሰቦች በመነሳትና የየአስተዳደር ዕርከኖችን ማህበረሰባዊና ህጋዊ አገልግሎቶችን በመንተራስ ቴክኒካዊና መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በጥናት ላይ ተመርኩዞ መዘርጋት ይገባዋል። ይኸም ማለት የኩነቶችን መከሰት የሚያረጋግጡ ህጋዊ የኩነት ምስክር ወረቀት መረጃዎች ለግለሰቦች ሊሰጥ ይገባል። በተጓዳኝ በቀበሌ መስተዳድር ደረጃና ከዚያም ዝቅ ባለ የማህበረሰብ ክፍል በተለይም ለጤናና የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ ምሪት የሚሰጡ ግለሰባዊና ቤተሰባዊ እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ የተጠቃለሉ መረጃዎች ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አጠቃቀም በሚያመች ሁኔታ መረጃዎችን ማዘጋጀትና ማቅረብ የሚያስችል አደረጃጀት ሊዘረጋ ይገባል። በተመሳሳይ እነዚሁ መረጃዎች በተለይም አሁን ሀገሪቱ ከምትከተለው ያልተማከለ የልማት አደረጃጀት አንጻር በወረዳ መስተዳድር ደረጃ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ሰፊ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። ለዚህም ዋነኛው መሰረት ከህዝብና ቤት ቆጠራ ጋር በመጣመር ትክክለኛና አስተማማኝ የህዝብ ብዛትና ምጥነት መረጃ በየዓመቱና ባነሰ ጊዜ ለወረዳ መስተዳድሮች ከምዝገባ ሥርዓቱ በሚገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ አማካይነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማዘጋጀት ማስቻሉ ነው።

ከላይ ጠቅለል ባለ መልኩ የተገለጹትን የየዘርፍ የመረጃ ፍላጎቶችን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ፣ ጊዜና የመረጃ አቅርቦት ደረጃ ለማዘጋጀት በማዕከልና በየአስተዳደር እርከኑ የሚቋቋሙ የምዝገባ ጽ/ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት ወሳኝ ድርሻ አለው። የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር የሀገሪቱን የፌደራል የመንግሥት አወቃቀር፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችንና መርሆዎችን እንዲሁም የሀገሪቱን የተቋማት አስተዳደራዊ አደረጃጀት ባገናዘበ የጥናት ውጤት ላይ በመመሥረት መከናወን ይገባዋል። በመሆኑም በረቂቅ አዋጁ የቀረበው የኩነቶች ምዝገባ ተቋማዊ አደረጃጀት እንደ ኮሚሽኑ ጽ/ቤት እምነት እንደገና በጥልቀት ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በተዘጋጀው የግምገማ ጥናት ሰነድ ላይ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ያልተማከለ አደረጃጀት ሊይዝ እንደሚገባና በማዕከል የሚቋቋመው የምዝገባ ጽ/ቤት በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባ ሥራውን በአመዛኙ በቴክኒኩ ዘርፍ የሚያስተባብርና ስታንዳርዶችን በማውጣት እንዲሁም የተለያዩ ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴዎችን በመከተል የምዝገባውን የሽፋንና የመረጃ ጥራት ደረጃ የሚቆጣጠር እንደሚሆን ነው። ይኸም ሀገር አቀፍ የምዝገባ ተቋም በመንግሥት የተሰጠው ሀላፊነትና ተግባር ከኩነቶች ምዝገባ ተግባር ጋር ቀጥታ ተዛምዶ ካለው ነባር ተቋም ጋር በመቀናጀት እንዲዋቀር ቢደረግ ከወጪና ሥራዎችን ከማቀናጀት አንጻር አመቺ ይሆናል የሚል አስተሳሰብ አለ። እንደረቂቅ አዋጁ አቀራረብ በየአስተዳደር ዕርከኑ የሚቋቋሙ የምዝገባ ጽ/ቤቶች ማለትም በክልልና ከክልል መስተዳድር በታች የሚዋቀሩት በሌላ ነባር ተቋም ሥር እንደሚደራጁ ሳይሆን የተለዩ ተቋማት እንደሚሆኑ በማሰብ የተዘጋጀ ነው። እንደኮሚሽኑ

ጽ/ቤት አስተሳሰብ በየክልል መስተዳድሩ አዲስ የምዝገባ ተቋማትን ማቋቋም የሀገሪቱ አቅም የሚፈቅድ ከሆነ የሚመረጥ ቢሆንም በእንጻሩ የነባር ተቋማትን የሥራና የሙያ ቅርበት በመገምገም የምዝገባ ተቋማቱን በነባር ተቋማት ሥር በማቋቋም ማደራጀት እንደአማራጭ ሊወሰድ እንደሚችል ያስገነዝባል። ይኸም ሲሆን የምዝገባውን ተግባር የሚያከናውነው የሥራ ዘርፍ የበጀትና የአሠራር ነጻነቱን በሚጠብቅ መልኩ የማቋቋሚያ ህጉ ሊቀረጽ ይገባል።

- በአንቀጽ 3 ስለማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት መቋቋም የተመለከተው ቀደም ሲል በአንቀጽ 1 በምዝገባ ሥርዓቱ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ላይ በመመርኮዝ የተሰጠውን አስተያየት የሚጋራ ስለሚሆን ከዚያ ጋር በተዛምዶ ቢታይ፤
- በአንቀጽ 3 ማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ ለፍትህ ሚኒስቴር እንደሚሆን ይገልጻል። በኢትዮጵያ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት "የተማከለ" አደረጃጀት የሚከተል ከሆነ የማዕከላዊው ምዝገባ ጽ/ቤት ተጠሪነት ለፍትህ ሚኒስቴር መሆኑ ተገቢ ሊያደርገው ይችል ይሆናል። ይኸም ቢሆን በፌደራል ደረጃ ለተዋቀረ ተቋም እስከ ቀበሌ መስተዳድር መዋቅሩን ዘርግቶ የምዝገባውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲያከናውን ማድረግ ተግባሩን አዳጋች ከማድረጉም በላይ ውጤታማም አይሆንም። በሌላም በኩል በኢትዮጵያ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት "ያልተማከለ" አደረጃጀትን ቢከተልም የምዝገባ ሥርዓቱ ከህግ ጠቀሜታው በበለጠ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ ለስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎትና በየአስተዳደር እርከኑ በተለይም በጤናና ትምህርት ግልጋሎት አሰጣጥ ካለው የዕለት ተዕለት የመረጃ ፍላጎት አንጻር የፍትህ ሚኒስቴር በዘርፉ በቴክኒካዊ ሥራዎች ልምዱ እንዲሁም አሁን ያለው ተቋማዊ አደረጃጀቱ (በተለይ ከክልል መንግስታት ጋር) ከሌሎች ተቋማት የተሻለ የሚሆንበት ምንም መመዘኛ ባለመኖሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋመውን ጽ/ቤት ለሚኒስቴሩ ተጠሪ ማድረግ የምዝገባውን ሥራ ውጤታማ አያደርገውም የሚል አስተሳሰብ አለ። በዚህ ረገድ ምናልባትም በአደረጃጀት በተለይም ከክልል መስተዳድራት ጋር ካለ ግንኙነት አንጻር ከፍትህ ሚኒስቴር ይልቅ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ለምዝገባው ሥራ የተሻለ አደረጃጀት እንዳለው ሊወሰድ ይችላል። ይኸም ሆኖ በሌላ በኩል የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በቴክኒክ፣ በተቋማዊ አደረጃጀት (በተለይም ከክልል መስተዳድራት ጋር ካለው መዋቅራዊ ግንኙነት)፣ ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን የማጠናቀርና የማሰራጨት ሀላፊነት የተሰጠው ተቋም መሆኑ እንዲሁም በማቋቋሚያ አዋጁ በሀገሪቱ የሕዝብና የቤቶች ምዝገባ እንዲቋቋምና እንዲደራጅ ሀላፊነት የተሰጠው ከመሆኑ አንጻር በማዕከል ሀገር አቀፍ የኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ጽ/ቤት ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ይመስለናል።
- አንቀጽ 4 በየክልሉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤቶች እንደሚቋቋሙ፣ እንደአስፈላጊነቱም በዞንና በወረዳ ሊቋቋሙ እንደሚችሉ ይደነግጋል። እዚህ ላይ በክልል መስተዳድር ደረጃ የምዝገባ ጽ/ቤቶች መቋቋማቸው ተገቢና አስፈላጊ ነው። እንደ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት እምነት የምዝገባ ሥርዓቱ ለልማትና አስተዳደር

ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች የሚያመነጭ ከመሆኑና ወረዳዎች የልማትና የአስተዳደር ማዕከል ከመሆናቸው አንጻር የምዝገባ ጽ/ቤት በወረዳ መስተዳድር እርከን መቋቋሙ ተገቢ ነው የሚል ሀሳብ አለ። ከዚህም በተጨማሪ ግለሰባዊ የኩነቶች መረጃዎች የአንድን ሀገር ነዋሪ ህጋዊ ማንነት አልፎም ዜግነቱን ጭምር የሚያረጋግጡ መረጃዎች ከመሆናቸው አንጻር የክብር መዝገብ ሹሞች ሊሾሙ የሚገባው በወረዳ የአስተዳደር ዕርከን ሊሆን ይገባል የሚል አስተሳሰብ አለ። በሌላም በኩል በተለይ የገጠር ቀበሌ መስተዳድሮች እንዲህ ዓይነት ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ህጋዊ መረጃዎች ለማጽደቅ የሚያስችል አቅም ያላጎለበቱ ስለሆነ የክብር መዝገብ ሹሞች ጽ/ቤት በወረዳ መስተዳድር ሥር እንዲቋቋም መደረጉ አስፈላጊ ነው።

- አንቀጽ 4 በከተሞች የኩነቶች ምዝገባ አደረጃጀት ምን ሊሆን እንደሚገባ አልጠቀሰም። አሁን የሚታየውና የወደፊት የከተሞች አስተዳደር ምሪት ከተሞች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር አቅም እያጎለበቱ እንደሚሄዱ የሚያመላክት ነው። ለኩነቶች ምዝገባ አሰራር ከተሞች አመቺ አደረጃጀት ያላቸው ከመሆኑ አንጻር የከተሞችን እድገትና ደረጃ በተከተለ መልኩ የምዝገባ ጽ/ቤትና የምዝገባ ሹሞች ሊኖራቸው የሚያስችል የህግ አንቀጽ በአዋጁ ሊካተት ይገባል።
- በአንቀጽ 4 በክልልም ሆነ በተዋረድ መስተዳድሮች የሚቋቋሙ የምዝገባ ጽ/ቤቶች የኩነቶች መዝገብ ቤት እንደሚኖራቸው አልተገለጸም። ከምዝገባ ሥርዓቱ በምዝገባ ክልሉ በየዕለቱ ስለሚከሰቱ ኩነቶች የተመለከቱ በርካታ ህጋዊ መረጃዎች ይደራጃሉ። እነዚህ ህጋዊ መረጃዎች በዘላቂነት የግለሰቦችን ማንነት የሚያረጋግጡ ከመሆናቸው አንጻር ለአጠቃቀም በሚያመችና ለመጥፋት ወይም ያላግባብ ለመጠቀም በማያጋልጥ አኳኋን ሊቀመጡበት የሚያስችል አደረጃጀት ሊዘጋጅ ይገባል። ስለሆነም የኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት በሚቋቋምበት ቦታ ሁሉ የኩነቶች መዝገብ ቤት ሊቋቋም ስለሚገባ በአዋጁ ይኸው ጉዳይ ቢካተት፣
- አንቀጽ 5 የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባርን የሚደነግግ አንቀጽ ነው። በመሰረቱ የጽ/ቤቶች ተግባርና ሀላፊነት አቀራረጽ የምዝገባ ሥርዓቱ ከሚከተለው አደረጃጀት ጋር የተቆራኘ ነው። ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የማዕከላዊው ጽህፈት ቤት ተግባር የምዝገባውን ቴክኒካዊ አሰራር በሀገር አቀፍ ደረጃ ማስተባበር፣ የአሰራር ቅንጅቶችን መፍጠር፣ ስታንዳርዶችን ማውጣት፣ ሞዴል የቴክኒክ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ፣ ዓለም አቀፍ ትብብሮችን ማድረግ፣ የሽፋንና የመረጃ ጥራት ግምገማዎችን ማድረግ፣ ስልጠናዎችን ማስተባበር፣ በዘርፉ ምርምሮችን ማድረግ እና የመሳሰሉ ተግባር ላይ የሚወሰን ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ በአንቀጽ 5 በተለይ ንዑስ አንቀጽ (ሀ)(ለ)(ሐ)(ቀ)(በ) መሻሻል የሚገባቸው ሲሆን በተጨማሪም በሚወሰነው አደረጃጀት ላይ በመመርኮዝ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ማካተት የሚገባ ይመስለናል።
- አንቀጽ 6 የክልል ጽህፈት ቤቶችን ስልጣንና ተግባር የሚደነግግ አንቀጽ ነው። የክልል የምዝገባ ጽ/ቤቶች ተግባርና ሀላፊነት የምዝገባ ሥርዓቱ አደረጃጀት የተማከለ ወይም

ያልተማከለ ከመሆኑ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። ይኸም ሆኖ በክልሉ ለሚከናወነው የምዝገባ ሥራ በመምራትም ሆነ በማስፈጸም፣ በጀት በመመደብና የበጀት አጠቃቀሙን በመወሰን፣ የሰው ሀይል ምልመላና አስተዳደር እንዲሁም የተቋማትን አወቃቀር ሊወስን የሚገባው የክልሉ የምዝገባ ጽ/ቤት ነው። ከዚህም በላይ የክልሉ ጽ/ቤት ከሀገር አቀፉ የምዝገባ ጽ/ቤት ጋር ትብብርና የሥራ ቅንጅት የመፍጠር እንዲሁም የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃን ለሚያጠናቅረው አካል በህጉ በሚደነግገው የጊዜ ገደብ በቀበሌ ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገቡትን የኩነቶች ስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን የማስተላለፍ ሀላፊነት አለበት።

- አንቀጽ 7 ስለሌሎች ጽ/ቤቶች ይመለከታል። ቀደም ሲል እንደተመለከተው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በወረዳ መስተዳድር ደረጃ የምዝገባ ጽ/ቤቶች መቋቋም እንደሚገባቸውና የክብር መዝገብ ሹም በወረዳ መስተዳድር ዕርከን ሊሆን እንደሚገባ ባሳሰበው መሰረት ተግባርና ሀላፊነታቸው ጭምር ተለይቶ ቢቀመጥ፣
- በተመሳሳይ በአንቀጽ 7 በከተሞች የምዝገባ ሥርዓቱ አደረጃጀት መለየትና የጽ/ቤቶቹ ስልጣንና ተግባር ተለይቶ ቢቀመጥ፣
- አንቀጽ 8 የቀበሌ ምዝገባ ጽ/ቤቶችን ስልጣንና ተግባር የሚመለከት ነው። ንዑስ አንቀጽ 1 የክብር መዝገብ ሹም በቀበሌ እንደሚኖር የሚገልጸው መዝጋቢ በሚል ቢተካ። በንዑስ አንቀጽ 2 በክብር መዝገቦች ላይ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን ብቻ ማካሄድ ሳይሆን መዝጋቢው በተጓዳኝ የኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን በተዘጋጁት ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾች ላይ ከመዝገቦች በመገልበጥና አስመዝጋቢውን በመጠየቅ መመዝገብ አንዱና ዋነኛው ተግባር ተደርጎ በህጉ መቀረጽ ይገባዋል። በንዑስ አንቀጽ 3 የምዝገባ ሰነድ ቅጂዎችን ብቻ ሳይሆን የኩነቶች ስታትስቲስ ሪፖርት ቅጾችን ለሚመለከተው እንደሚያስተላልፍ ቢካተት። የቀበሌ ምዝገባ ጽ/ቤቶች ለህብረተሰቡ ቅርብ የሆኑና በምዝገባ ክልሉ የተከናወኑ ኩነቶችን ነዋሪዎች በህጉ በተቀመጠው ጊዜ እንዲያስመዘግቡ በማድረግ በተለይም ተከታታይና ቋሚ ትምህርት የመስጠት ሀላፊነታቸው መገለጽ ይገባዋል። ከዚህም በላይ የምዝገባ ሽፋኑን የተሟላ ለማድረግ በየተወሰነ ጊዜ በየቤተሰቡ በመሄድ የተዘለሉ ኩነቶች ላለመኖራቸው ማረጋገጥ እንደሚገባቸው መገለጽ ይገባዋል። በምዝገባ ጽ/ቤቱ የሚከናወኑ ለምሳሌ መረጃዎችን ማደራጀትና በሚስጥር መጠበቅ፣ በአካባቢ አስተዳደር ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ መረጃዎችን ለተፈቀደላቸው መረጃ ጠያቂዎች መረጃ መስጠትን እና ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎችን ማከናወን እንደሚገባቸው መገለጽ ይገባዋል። በቀበሌ ደረጃ የሚቀመጡ መዝጋቢዎች የምዝገባውን ተግባር የሚያጠናክሩና ከመስተዳድሩ ጋር የሚያቀናጁ ተጓዳኝ ተግባራትን ለምሳሌ የነዋሪነት መታወቂያ የማዘጋጀት፣ . . . የመሳሰሉትን አቀናጅተው የሚሰሩበትን አደረጃጀት በሚያመለከት መልኩ ተግባርና ሀላፊነታቸው ቢቀረጽ።

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ሥር የተካተቱት አንቀጾች የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ካቀረበው የግምገማ የጥናት ሰነድና በዘርፉ በጥናት መልክ አስተያየት ሊያቀርቡ በሚችሉ ተቋማት ወይም

ባለሙያዎች መረጃ ላይ በመመርኮዝ እንደገና በጥልቀት መታየት እንደሚገባው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እምነት ነው።

## 9. ምዕራፍ ሦስት - ስለክብር መዝገብ ሹሞች

- በአንቀጽ 9(1) የተመለከተው ከላይ በምዕራፍ ሁለት ከተገለጸው አስተያየት ጋር በመገናዘብ የሚወሰን እንደሚሆን፣
- በአንቀጽ 9(2) ስለክልል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽሕፈት ቤቶች ሀላፊዎች አሿሿም የተመለከተው ምንም እንኳ ከላይ ስለአደረጃጀት በተሰጠው አስተያየት ላይ የሚመሰረት ቢሆንም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓቱ ስለእያንዳንዱ ግለሰብ የዜግነትና መሳይ ሀገራዊ ይዘት ያላቸው ህጋዊ መረጃዎችን የሚያስገኝ ከመሆኑ አንጻር የምዝገባ ጽ/ቤት ሀላፊዎች የመንግሥት የሀላፊነት ደረጃቸውን በሚለይ መልኩ መደንገግ ይገባዋል። በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ባዘጋጀው ሰነድ ላይ በዝርዝር የተገለጸ ቢሆንም በጥቅሉ ግን የምዝገባ ጽ/ቤት ሀላፊዎች በየደረጃው ያሉ የሥራ አስፈጻሚ አባል ሊሆኑ እንደሚገባ ለማሳሰብ እንወዳለን።
- በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 9(3) በቀበሌ መስተዳድር ደረጃ የክብር መዝገብ ሹም እንደሚኖር አልፎም እንደአስፈላጊነቱ ረዳት የክብር መዝገብ ሹሞች በቀበሌ መስተዳድሮች ሥር ሊሾሙ እንደሚችሉ ተመልክቷል። በመሰረቱ የክብር መዝገብ ሹሞች በምዝገባ ሥርዓቱ ትልቁን የመንግሥት ሀላፊነት የሚሸከሙና የመንግሥትን ውክልና የሚቀበሉ ግለሰቦች ናቸው። የክብር መዝገብ ሹሞች በሙያ ብቃታቸውና በተለይም በስነ-ምግባራቸው ከፍተኛ እምነት የሚጣልባቸው ሊሆኑ ይገባል። ከዚህም በላይ የክብር መዝገብ ሹሞች ለዜጎች የዜግነት ሰነድ በማዘጋጀትና የመረጃውን ህጋዊነት የሚያረጋግጥ መረጃ በመስጠት ረገድ የመንግሥትን ውክልና የሚወስዱ ሊሆኑ ይገባል። ከበርካታ ሀገሮች የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ልምድ እንደሚታየው የክብር መዝገብ ሹሞች ከንቲባዎች፣ አስተዳዳሪዎችና በተመጣጣኝ ከፍተኛ የመንግሥት ሀላፊነት የተቀበሉ ግለሰቦች ናቸው። ይኸም በመሆኑ የክብር መዝገብ ሹሞች ከፍ ባለ የአስተዳደር እርከን ላይ የሚገኙ የመንግሥት የሥራ ሀላፊዎች ሊሆኑ ይገባል። በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ባዘጋጀው ሰነድ የክብር መዝገብ ሹሞች በወረዳ መስተዳድርና በከንቲባዎች ደረጃ መፈጸም እንዳለበት ተገልጿል። በቀበሌ መስተዳድር ደረጃ በሚቋቋሙ ጽ/ቤቶች የምዝገባውን ተግባር የሚፈጽሙ መዝጋቢዎችን መመደብና የዕለት ተዕለት የምዝገባ ሥራውን እንዲፈጽሙ በማድረግ የማጽደቁን ሀላፊነት ከፍ ባለ የአስተዳደር ዕርከን ላይ የሚገኙት የክብር መዝገብ ሹሞች እንዲፈጽሙ ማድረግ ይገባል።
- በአንቀጽ 13(1) በኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላ ጽ/ቤቶች የኩነቶች ምዝገባ እንደሚደረግና የኤምባሲው ወይም ቆንሲላ ጽህፈት ቤቱ ከቋሚ ሰራተኞቹ ማናቸውንም አንድ ሰራተኛ እንደሚመድብ ይገልጻል። በዚህ ሂደት ተጨማሪ መመዘኛ ሆኖ የቀረበው ሰራተኛው ቋሚ መሆኑ ብቻ ነው። በመሰረቱ ይህ የህግ አቀራረጽ መሰረታዊ የሙያ ግንዛቤ ግድፈትን የሚያመለክት ነው። ቀደም ሲል ስለክብር መዝገብ ሹሞች በአጭሩ ለመግለጽ

እንደተሞከረው በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በምዝገባው የሚገኙ ህጋዊ መረጃዎች ጥቅምና ደረጃ በእኩል መታየት ይገባዋል። በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች በምዝገባ ሥርዓቱ የሚኖራቸው ደረጃና ከሀገር አቀፉ የምዝገባ ጽ/ቤት ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት በጥልቀት መመርመርን ይጠይቃል። ስለሆነም ይኸ አንቀጽ እንደገና ከመሠረቱ ሊታይ የሚገባ ይመስለናል።

- በአንቀጽ 13(2) የቀረበው አገላለጽ ግልጽነት የጎደለው ነው። በተለይም "ያገባናል" የሚለው ቃል የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው ለማለት ይሁን ሌላ ግልጽ አይደለም።
- በአንቀጽ 13(3) በኤምባሲዎች ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤቶች የሚገኙ የመዝገብ ቅጅዎች ወደ ማዕከላዊ መዝገብ ቤት በየተወሰነ ጊዜ የሚላኩበት ሥርዓት መኖሩ ግድ ነው።
- አንቀጽ 14 በመርከብ ላይ ስለሚከሰቱ ኩነቶች አመዘጋገብ የሚመለከት ነው። በረቂቁ የመርከብ አዛዦች በመርከቦቻቸው ውስጥ ለሚከሰቱ ኩነቶች የክብር መዝገብ ሹሞች እንደሆኑ ይገልጻል። ሆኖም ተግባራቸው መመዝገብ ሳይሆን ማስታወቅ ነው። የማስታወቅ ተግባር (Informant) በኩነቶች ምዝገባ አሰራር ከክብር መዝገብ ሹም ተግባር የተለየ ነው። ስለሆነም በዚህ አንቀጽ በመርከብ ላይ ስለሚከሰቱ ኩነቶች አመዘጋገብ የተገለጸው ከምዝገባ ሥርዓቱ አደረጃጀት ጋር ተገናዝቦ ቢቀርብ፤

## 10. ምዕራፍ አራት - ስለመመዝገብ

በዚህ ምዕራፍ ሥር የኩነት መዝገቦች የሚይዟቸው መረጃዎች ዓይነት ተመልክቷል። የኩነት መዝገቦች ይዘት የመለየቱ ሥራ በተለይም በምዝገባ ሥርዓቱ ሊገኙ የሚገቡ ህጋዊ፣ አስተዳደራዊና የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች የአመዘጋገብ ዘዴ ጋር በማያያዝ በጥናት ላይ ተመርኩዞ መወሰን ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ በስፋት ማየት፣ አጠቃላዩን የምዝገባ ሥርዓቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የመረጃዎችን ማስተላለፍ ሥርዓትና የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት በማገናዘብ የመዝገቦችን ይዘት መወሰን ያስፈልጋል። በተለያዩ ሀገሮች የተለያየ የአሰራር ልምድ ቢኖርም በአመዛኙ የሚዘወተሩት ሁለት የመዝገብ አዘገጃጀት መንገዶች ናቸው። አንደኛው በኩነቶች መዝገብ የህግና የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎችን አጣምሮ መዝገቡን የማዘጋጀት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎችን ከመዝገቡ በማወራረስና አስመዝጋቢውን በመጠየቅ ለብቻ በተዘጋጀ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን የማዘጋጀት ነው። በመጀመሪያው አሰራር አንድ የክብር መዝገብ ሁሉንም የምዝገባ ሥርዓቱን የመረጃ ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ የሚዘጋጅበት ሲሆን በሁለተኛው አሰራር ለኩነቱ አንድ መዝገብና ለስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ መመዝገቢያ ደግሞ ሌላ የኩነት ስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጽ እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። በቀረበው ረቂቅ ህግ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች ስለሚሰበሰቡበት የአመዘጋገብ ዘዴም ሆነ ስለመረጃዎቹ ዓይነት ምንም አልተገለጸም። በሌላም በኩል በመዝገቦቹ እንዲካተቱ ከተገለጹት መረጃዎች ውጭ ሌሎች አስፈላጊነታቸው የታመነባቸው መረጃዎች ስለሚካተቱበት መንገድ በህግ ረቂቁ አልተገለጸም። ከዚህም አልፎ በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ

አወቃቀር በመዝገቦች አደረጃጀትና በመረጃዎች ዓይነት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እንደሚኖረው በማገናዘብ የመረጃዎች ዓይነት አልተለዩም። ስለሆነም የልደት፣ የጋብቻ፣ የፍቺና የሞት ኩነቶች የመዝገብ ይዘት ሰፋና ጠለቅ ባለ መልኩ ከተለያዩ ሙያዎችና የመረጃዎች ፍላጎት/አጠቃቀም አንፃር ሊታይ ስለሚገባ በዚህ ረገድ በአንቀጽ 15(2) ስለልደት መዝገብ ይዘት፣ በአንቀጽ 22 ስለጋብቻ መዝገብ ይዘት፣ በአንቀጽ 27(2) ስለሞት መዝገብ ይዘት የተመለከተው እንደገና ሊታይ ይገባል።

በሌላም በኩል በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር የአንድን ኩነት መከሰት የማሳወቅና የማስመዝገብ ሥራ ልዩነትን በግልጽ ከመብትና ግዴታ ጋር በማዛመድ መግለጽ ያስፈልጋል። የአንድን ኩነት መከሰት ያወቀ ግለሰብም ሆነ ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት ማሳወቅ እንደሚገባ በጥቅሉ መደንገግ ቢቻልም፣ እንደየኩነቱ ባህርይ ተለይተው የማሳወቅ ግዴታ የሚጣልባቸውን ግለሰብም ሆነ ድርጅት ለይቶ በህጉ ማስቀመጥ ግን የግድ ነው። እነዚህ የማሳወቅ ግዴታ የተጣለባቸው በህጉ የግዴታቸው መጠን በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል። በሌላ በኩል የአንድን ኩነት መከሰትና ስለኩነቱ ባህርያት በምዝገባ ጽ/ቤት በመሄድ የማስመዝገብ ግዴታ የሚጣልባቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ተለይተው በህጉ መቀመጥ አለባቸው። እዚህ ላይ የማስታወቅና የማስመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ግለሰቦች ከህግ አንፃር በጣም የተለያዩ መሆናቸው ግልጽ ሊሆን ይገባል። በቀረበው ረቂቅ ላይ የማስታወቅና የማስመዝገብ ተግባራትን ከጽንሰ-ሀሳብ ጀምሮ መለያ ካለመደረጉም በላይ በምዝገባ አፈጻጸም ሥርዓቱም የእነዚህ ተግባራት አንድነትና ልዩነት በግልጽ አልተቀመጠም። ከዚህ አንፃር አንቀጽ 16፣ አንቀጽ 23 እና አንቀጽ 28 እንደገና ሰፋ ተደርገው ሊታዩ ይገባል።

በህግ የተቀመጠው የምዝገባ ጊዜ ቢያልፍም ኩነቶች መመዝገብ እንዳለባቸው በረቀቅ አዋጁ ተገልጿል። ሆኖም በህግ ከተቀመጠው የምዝገባ ጊዜ የዘገዩ ምዝገባዎች የመረጃ ደረጃቸው ምን መሆን እንደሚገባው አልተገለጸም። ስለሆነም በአንቀጽ 18 (በልደት መዝገብ)፣ አንቀጽ 25 (ቢጋብቻ መዝገብ) እና በሞት መዝገብ የተለያዩ አንቀጾች የተመለከተው የዘገዩ ኩነቶች አመዘጋገብ በተለይም መረጃዎቹ ከሚያስገኙት የህግና የስነ-ህዝብ መረጃ አንጻር እንደገና ሊታይ ይገባል።

## 10.1 የልደት መዝገብ

- በአንቀጽ 15(1) "መወለድ" የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በሙያዊ አገላለጽ ሁለት ክስተቶችን በሚያመለክት መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "መወለድ" በህይወት መወለድን ወይም ሞቶ መወለድን ሊያመለክት ስለሚችል በህጉ በሚሰጠው ትርጓሜ መሰረት አንቀጹ ሊሻሻል ይገባል። በረቂቁ የተገለጸው የልደት ምዝገባ ጊዜ (ስድሳ ቀናት) ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኘው መረጃ ሊሰጥ የሚገባውን ጥቅም ያገናዘበ አይደለም። ኩነቶች እንደተከሰቱ የሚመዘገቡበት ፍጥነትና የጊዜ ገደብ የመረጃውን የህጋዊነት ደረጃ ከመወሰኑም ባሻገር ምዝገባው በሽፋኑና

በጥራቱ የሚጠበቀውን ደረጃ ለማሙዋላቱ የመጀመሪያ መለኪያ መስፈርት ነው። በመርህ ደረጃ ማናቸውም ኩነት በተከሰተ አጭር ሰዓታት መመዝገብ ይገባዋል። በዚህ ረገድ በኢኮኖሚ የበለጸጉ ሀገሮች የጤና አቅርቦታቸውና ሽፋኑ የተሟላ በመሆኑ በነዚህ ሀገራት ለምሳሌ ልደት በተከሰተ ዕለት በጤና ተቋማት እንዲመዘገብ ይደረጋል። እንዲህ አይነት አሰራር በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ መፍጠር እንደማይቻል ግልጽ ቢሆንም ልደት በህጉ የሚሰጠው የመመዝገቢያ ጊዜ ከአንድ ወር ሊበልጥ አይገባም። እዚህ ላይ የምዝገባውን የጊዜ ገደብ በመከተል ልደቱን በወቅቱ የማስመዝገቡን አሰራር የሚወስነው የምዝገባ ጽ/ቤቶችን ለህብረተሰቡ ቅርብ በሆኑ ቦታዎች ላይ የማቋቋሙ ሥራና በየጊዜው ስለምዝገባው ጥቅምና አስፈላጊነት በህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር በሚደረገው ጥረት ላይ ነው።

- በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ የልደት ኩነት ከሚያስገኘው ጠቀሜታና የሰው ልጆች የህጋዊነት ምንጭ ከመሆኑ አንጻር በምዝገባ አፈጻጸሙ የተለየ ጥንቃቄና ትኩረትን ይጠይቃል። በተለይም በእናቶችና ህጻናት መብት ጥበቃና ወቅታዊ አገልግሎት በመስጠት የምዝገባው የጊዜ ገደብ መጥበብ የግልጋሎቱን ተፈጻሚነት የበለጠ የሚያጎላው ስለሆነ ህጉ የጊዜ ገደቡን ለማጥበብ የሚያስችሉ አሰራሮችን በሚያበረታታ አኳኋን ቢቀረጽ የተሻለ ይሆናል።
- በልደት መዝገብ የሚመዘገቡ መረጃዎች ዓይነት በአንቀጽ 15(2) ተመልክቷል። በንዑስ አንቀጹ ከተገለጹት በተጨማሪ ልደቱ የተመዘገበበት ቀንና ልደቱ የተከሰተበት ቦታ፣ ልጁ በጋብቻ ውስጥ ወይም ውጪ ስለመወለዱ፣ የልደቱ ዓይነትና በልደት ጊዜ ክብደት እንዲሁም በተለይ ስለህፃኑ/ኗ እናት ባህርያት የተመለከቱ መረጃዎች በመዝገቡ ሊካተቱ ይገባል።
- በአንቀጽ 20 የተጠቀሱት ክስተቶች በራሳቸው ኩነቶች ናቸው። የእነዚህ ኩነቶች አመዘጋገብ ሥርዓትና የሚመዘገቡ መረጃዎች ዓይነት ለማናቸውም የመረጃዎች አጠቃቀም በሚያመች መልኩ መደንገግ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የሌሎች ሀገሮችንም ልምድ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል።

## 10.2 ስለጋብቻ መዝገብ

- ስለጋብቻ አፈጻጸም በተለያዩ ህጎች የተገለጹ ድንጋጌዎች እንዳሉ ይታወቃል። ለምሳሌ የጋብቻ እድሜ፣ ፈቃደኝነት፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ (የቀድሞ ጋብቻ)፣ . . . ወዘተ ጉዳዮች በምዝገባው ወቅት መዝጋቢው ሊያደርግ ስለሚገባው ጥንቃቄና መሙዋላት የሚገባውን ሁኔታዎች በማጣራት በኩል እንዲሁም በየክልል መስተዳድሩ በጋብቻ አፈጻጸም የህግ ሥርዓቶች የሚኖሩ ልዩነቶችን እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባ ለአፈጻጸም በሚያመች መልኩ በግልጽ በህጉ ማስቀመጥ ይገባል። በዚህ ረገድ በአንቀጽ 21ም ሆነ በሌሎች አንቀጾች ይኸው ሁኔታ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል።
- የክብር መዝገብ ሹም እንዱ ተግባር የሲቪል ጋብቻ ሥርዓትን ማስፈጸም ነው። ይኸው ተግባር ከላይ የተገለጹ ሁኔታዎችን ባገናዘበና ለአፈጻጸም ግልጽ የህግ መመሪያዎችን ባዘለ መልኩ በረቂቅ ህጉ አልተቀመጠም።

- በአንቀጽ 22 የጋብቻ መዝገብ ይዘት ተመልክቷል። በረቂቁ የተመለከቱት መረጃዎች ከመዝገብ ወደ ምስክር ወረቀት የሚተላለፉ መረጃዎችን እንጂ በክብር መዝገቡ ሊካተቱ የሚገባቸውን በተሟላ ሁኔታ የሚያመለክት አይደለም። ስለሆነም የተጋቢዎች መደበኛ መኖሪያ፣ የቀድሞ ጋብቻ ሁኔታ፣ የትምህርትና የሥራ ሁኔታ እንዲሁም ጋብቻው የተፈጸመበት ሥፍራና ቀን መካተታቸው ግድ ነው።
- የአንቀጽ 24(2) አጻጻፍና አገላለጽ ጥንቃቄ የጎደለው የግንዛቤ ጉድለት ያለበት ጭምር ይመስላል። የክብር መዝገብ ሹም ወይም መዝጋቢው የኩነቱን መከሰት እንዳወቀ መመዝገብ እንደሚገባው ቢታወቅም ስለኩነቱ የሚመለከቱ መረጃዎችን ማግኘት የሚገባው ግን ኩነቱን የማስመዝገብ በህግ ግዴታ ከተጣለበት ወይም ከተጣለባቸው ግለሰቦች ብቻ መሆኑ በአንክሮ በረቂቁ ሊገለጽ ይገባ ነበር። የንዑስ አንቀጹ አገላለጽ አስመዝጋቢዎቹ ለመፈረም እንጂ መረጃውን ለመስጠት እንደሚፈለጉ አይገልጽም።
- አንቀጽ 26 ስለፍቺ መከሰት ማስታወቅን (ምዝገባን ሳይሆን) የሚመለከት ነው። ቀደም ሲል ስለፍቺ የተሰጠው አስተያየት እንዳለ ሆኖ በዚህ አንቀጽ የሚመዘገቡ ፍቺዎች በተብራራና በተገለጸ አኳኋን የፍቺ ዓይነቶች አልተገለጹም። በተለይም ከህግና ከስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎት አንጻር ፍቺ በረቂቅ ህጉ ተገቢው ትኩረትና በአመዘጋገብ አፈጻጸሙ ሊገጥሙ የሚችሉ የተወሳሰቡ ችግሮችን በአገናዘበ መልኩ አልተቀመጠም። በሀገራችን ወደ ፍርድ ቤት የሚሄዱ ፍችዎች በጣም ጥቂት እንደሆኑና አብዛኛው ፍቺ በባህላዊና በመንደር የሚከናወን ነው። በህብረተሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ትክክለኛ የፍቺ መረጃዎችን ለማግኘት የፍቺ ምዝገባ አሰራር ከጠበበው የህግ እይታ ሰፋና ጠለቅ ካለው የመረጃ ፍላጎት አንጻር ቢታይ የተሻለ ነው።

## 10.3 ስለ ሞት መዝገብ

የሞት ኩነት መረጃዎች እንደ ልደት ኩነት ሁሉ በተለይ በስነ-ህዝብ እና ጤና አገልግሎት መረጃ አቅርቦት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ከህግ አንጻር የልደትና የሞት ኩነት የምዝገባ መረጃዎች የሚፈለጉበት አግባብና በስነ-ህዝብና ጤና ዘርፍ የሚፈለጉበት ጊዜ፣ መጠንና የመረጃ የጥራት ደረጃ በጣም የተለያየ ነው። ለምሳሌ በወንጀል ነክ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች የሞቱ ሰዎች መረጃ ከህግ አንጻር የፍላጎቱ መጠን ዝቅተኛ ሲሆን በአንጻሩ በስነ-ህዝብ እና ጤና ዘርፎች የመረጃው አስፈላጊነት ዋነኛው የትኩረት መሰረቱ በዚህ የዕድሜ ክልል ላይ የሚያተኩር ነው። በአጠቃላይ በሞት ኩነት ምዝገባ የሚካተቱ መረጃዎች ዓይነት፣ የጽንሰ-ሀሳቦች ትርጉምና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ከህግ ፍላጎት በሰፋ መንገድ መታየትና የዘርፎችን ፍላጎት ባካተተ መልኩ መቃኘት ይገባዋል።

- በአንቀጽ 27(2) በሞት መዝገብ የሚካተቱ መረጃዎች ዓይነት ተመልክቷል። ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ የሟች ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዜግነት፣ የሞት ምክንያት፣ የሞተበት ስፍራ፣ የሞት የሀኪም ማስረጃ፣ የምስክሮች ማንነት፣ . . . ወዘተ ሊካተቱ ይገባል። በተለይ የሞት ምክንያት መረጃን መሰብሰብ ከመዝጋቢው በተጨማሪ ሌሎች ተቋማትንና የሙያ ዘርፎችን

ተሳትፎ በኦፕሬሽን ሥራው ውስጥ ማካተት የሚገባ በመሆኑ ይኸው ጉዳይ በህጉ የሚካተትበት አሰራር ቢገለጽ።

- በአንቀጽ 31 በግዳጅ ላይ ያሉ ወታደሮችን ሞት ማስታወቅ የሚገባው ክፍሉን የሚያዘው ሹም እንደሆነ ቢገልጽም፣ ይኸ ግለሰብ ስለኩነቱ መከሰት ለየትኛው አካል ለምሳሌ ለመከላከያ ሚ/ር፣ ለምዝገባው ጽ/ቤት፣ . . . ወዘተ ማስታወቅ እንዳለበት በግልጽ አያመለክትም። ከዚህም በላይ ስለመረጃው ሚስጢራዊነትና አጠቃቀም የተገለጸ ጉዳይ የለም።
- አንቀጽ 33(2) እና በአንቀጽ 36(2) ከኩነቶች ምዝገባ አሰራር አንጻር ግልጽ አይደሉም። በፍርድ ቤት የተሰጠ ማናቸውም ውሳኔ በክብር መዝገብ መመዝገቡ ግድ ሆኖ እያለ ይኸ አገላለጽ የምዝገባ አሰራሩን የማይቃረን መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል።
- በአንቀጽ 37 የተጠቀሱት ንዑስ አንቀጾች አጻጻፍ በተለይ የጠለቀ የህግ እውቀት ለሌለው የምዝገባ ሰራተኛ ግልጽ አይደለም። ከምዝገባ ሥራ ጋር ተገናዝበው ቢቀርቡ በአተገባበር ወቅት በቀላሉ መረዳት ይቻል ነበር።
- አንቀጽ 38 ከምዝገባ ሥራ ጋር ተገናዝቦ አልቀረበም። ፍርድ ቤቱ ከሻረው በኋላ ምዝገባው በማንና እንዴት ይከናወናል የሚለው አልተገለጸም።

## 11. ምዕራፍ አምስት - ስለ ክብር መዛግብት

- በአንቀጽ 39 የፍቺ መዝገብ ሊጨመር ይገባል።
- በአንቀጽ 40 የተመለከተው የክብር መዝገቦች ሥርጭትና ዝግጅት ከአጠቃላይ የምዝገባ ሥርዓቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት ጋር ተያይዞ መታየት ይገባዋል። ይኸውም ለምሳሌ ባልተማከለ የምዝገባ ሥርዓት ሞዴል መዝገቦች በማዕከል ተዘጋጅተውና እነዚያን ሞዴሎች በመከተል የክልል ምዝገባ ጽ/ቤት የየክልል የክብር መዝገቦችን እንዲያዘጋጁ ሊደረግ ይችላል። ይኸም ሲሆን ለመረጃ አጠናቃቀር፣ ተመሳሳይነትንና በማናቸውም መስተዳድር የክብር መዝገብ ሊያዙ የሚገቡ መረጃዎችን በመለየት፣ . . . ወዘተ የክልል መስተዳድሮችን የተለየ ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ የመዝገቦች አዘገጃጀት በህጉ ጭምር እንዲካተት ማድረግ ይቻላል። ስለሆነም የመዝገቦች ሥርጭትን የሚመለከተው ይኸ አንቀጽ ሰፋ ባለ መልኩ እንደገና ሊታይ ይገባል።
- በአንቀጽ 43 ስለመዝገቦች ዓይነት የተመለከተው የምዝገባ ሥርዓቱ ጥራዞችን እንደሚጠቀም በማሰብ ተዘጋጅቷል። መዝገቦች በተለያየ መልክ ሊዘጋጁ ይችላሉ። በአብዛኛው በጥራዝ ወይም በብትን ሊዘጋጁ ይችላሉ። የጥራዝ ወይም ብትን የምዝገባ ዶኩመንቶች አዘገጃጀት የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉዋቸው። የመዝገቦችን አይነት ለመወሰን የመረጃዎችን አጠቃቀም፣ ለመረጃ አጠናቃቀር ያላቸው አመቺነት፣ ለማስተላለፍ ያላቸው አመቺነትና ተመሳሳይ ጉዳዮችን በማካተት በጥናት ላይ በተመሰረተ መልኩ መወሰንን ይጠይቃል።
- ከላይ በአንቀጽ 43 ላይ የተሰጠውን አሰራርና አስተያየት መሰረት በማድረግ የቅጂዎችን ብዛት እንዲሁ ከአጠቃቀም አንፃር ታይቶ በጥንቃቄ ታስቦ ሊወሰን የሚገባ ነው። ስለሆነም በአንቀጽ 44 እና 45 የስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎትን እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል

ካለመገለጹም በላይ አሁን ያለውን የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ጭምር ያገናዘበ አይደለም።

- አንቀጽ 45 እንደ ኮሚሽኑ ጽ/ቤት ግንዛቤ የረቂቅ ህጉን የምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት እንደገና መፈተሽ እንደሚገባ የሚያስገድድ ነው። አንቀጹ የየኩነት የክብር መዝገብ ቅጂዎችን ኩነቱ ለሚመለከተው ግለሰብ በማስረጃነት እንዲሰጥ ያዛል። በዚህ ረገድ ኩነቱ ለሚመለከተው ግለሰብ በማስረጃነት የመስጠት የተለመደው አሰራር ከመዝገቦች ላይ የተወሰኑ መረጃዎችን ባካተተ መልኩ በተለይም ስለ ኩነቱ መከሰት የሚያረጋግጡ መረጃዎችን የያዘ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት የሚሰጠው ነው። ቀደም ሲል ስለ ኩነቶች ምስክር ወረቀት የተሰጠው አስተያየት እንዳለ ሆኖ በረቂቅ ህጉ የመዝገቦችን ቅጂ በማስረጃነት ለግለሰቦች የመስጠት አሰራርን ለመተካት ታስቦ የገባው እንደኢትዮጵያ ገና ጅምር ላይ ላሉ ሀገሮች ቀርቶ በኢኮኖሚ የበለጸጉትና የበርካታ ዘመን የምዝገባ አሰራር ልምድ ያላቸውም እያደረጉት አይመስለንም። በመሆኑም ይኸ አንቀጽ እንደገና በጥልቀት ሊጤን የሚገባው ይመስለናል።
- አንቀጽ 48 ከአደረጃጀት አንጻር ሊታይ ይገባል።
- በአንቀጽ 49(3) ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተሰጠው ሀላፊነት ሚኒስቴሩ በምዝገባ ሥርዓቱ ከተሰጠው የሥራ ድርሻ ጋር የተገናዘበ ካለመሆኑም በላይ የምዝገባውን ሥራ በተደራቢነት እንዲሰራው በተፈለገና እንደቀላል ሀላፊነት በማየት የተቀመጠ የህግ አንቀጽ ነው።
- አንቀጽ 50 በመረጃ አያያዝና ጽህፈት ሥራ አሁን እየታየ ያለውን የቴክኖሎጂ ዕድገት ባገናዘበ መልኩ ቢቀመጥ የተሻለ ነው። በዚህ ረገድ በተለይ በክልሎች መሀከል ያለውን የእድገት ልዩነት አላገናዘበም። ይኸ አንቀጽ በመረጃ አሞላል ጥንቃቄ የሚሹ ሃሳቦችን ለምሳሌ አስመዝጋቢውን በመጠየቅ መዝጋቢው መረጃውን መሙላት እንደሚገባው፣ ከመዝጋቢው በስተቀር ሌላ ሰው በመዝገቦቹ ላይ ምዝገባ ማከናወን የተከለከለ መሆኑን፣ በመዝገቡ ላይ ለተሞላ ማናቸውም መረጃ መዝጋቢውና አስመዝጋቢው በጣምራ ተጠያቂ መሆናቸውን፣ . . . ወዘተ ቢያካትት መልካም ነው።
- በክብር መዝገብ ውስጥ ጽሁፎች በሚመዘገቡበት ወቅት ስህተቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ይታወቃል። የስህተቶቹም ዓይነት ከባድ ወይም ቀላል የአጻጻፍ ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ። በአንቀጽ 58 ማናቸውም ስህተት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ እንዲታረም ይጠይቃል። የረቂቅ ህጉ በዚህ ጉዳይ ጥብቅ የመሆኑ ምክንያት ግልጽ ቢሆንም ከአፈጻጸም አንጻር በምዝገባ ጽ/ቤቱ የሚስተካከሉ ቀላል ስህተቶችን ፍርድ ቤት እየወሰዱ እንዲስተካከሉ የማድረግ አሰራርን መከተል አዳጋችና አላስፈላጊ ነው። ስለሆነም የፍርድ ቤት ትዕዛዝን የሚፈልጉና በቀላሉ በምዝገባ ጽ/ቤቱ ሊስተካከሉ የሚችሉትን ለይቶ በህጉ ማስቀመጥ የግድ ይላል። በዚህ ረገድም የሀገሮችን ተሞክሮ በጥልቀት ማየቱ አስፈላጊ ነው።
- በአንቀጽ 61(1) ሌሎች ስህተቶች የተባሉት ምን ዓይነት ሊሆኑ እንደሚችሉ ለአፈጻጸም ግልጽ በሆነ መልኩ ተለይተው ቢገለጹ።
- በክፍል አራት ርዕስ ላይ የተገለጸው ማለትም "በከፊል ተገልብጠው ስለሚወሰዱ መረጃዎች" የተባሉት ከምስክር ወረቀት የሚለዩ ካልሆነ በተለመደውና ግልጽ በሆነ መልኩ በህጉ ቢገለጹ፣

የሚለዩም ከሆነ የኩነቶች ምስክር ወረቀት አስፈላጊነትና እንዴት እንደሚዘጋጁ ተለይቶ በህጉ መካተት ስለሚገባው ረቂቁ ሁኔታውን እንዴት እንዳለፈው ግልጽ አይደለም። በርግጥ በአንቀጽ 65 ሥር የመዝገቡ ክፊልና ሙሉው ኮፒ አሰጣጥ ተመልክቷል፡ ሆኖም ንዑስ አንቀጾቹ ለምን ጉዳይ ሊዘጋጁ እንደሚገባ አይገልጹም። በሌላ መልኩ በአንቀጽ 66 ከሞት መዝገብ ክፊል ኮፒ ሊዘጋጅ እንደሚችልም አልተገለጸም።

- በክፍል አምስት "ምትክ ሰነድ" የሚል የቃላት አገላለጽ በተሻለና ግልጽ በሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ቢተካ፤
- በአንቀጽ 79 ሥር በፍትሀብሄር ህጉ አንቀጽ 1-47 የተገለጹት ከምዝገባ ሥርዓቱ አፈጻጸም ጋር በማይቃረን መልኩ እንዴት እንደሚተገበሩ የሚገለጽበት ወይም እነዚህ አንቀጾች የሚሻሻሉበት ሁኔታ መገለጽ ይገባዋል፤
- በአንቀጽ 80 የአስፈጻሚ አካላት እስከሚቋቋሙ ድረስ እስካሁን ሲሰሩ የነበሩ የሥራ ክፍሎች ይኸንን ህግ ተከትለው እየሰሩ እንዲቆዩ ተመልክቷል። በመሰረቱ ይኸንን ህግ የሚያስፈጽሙ አካላትን የማደራጀቱ ሥራ ሊፈጅ የሚችለው ጊዜና የጥሪት ፍላጎት በኢትዮጵያ የኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በሚከተለው አስተዳደራዊና መዋቅራዊ አደረጃጀት ላይ ይመሰረታል። ይኸም ሆኖ ህጉ ከወጣ በኋላ አስፈጻሚውን አካል ለማደራጀት በሚፈልገው ጊዜ ምክንያት በነባር ተቋማዊ አደረጃጀት ሥራውን ለመሥራት የሚያስገድድ ምክንያት ሊኖር ይገባል የሚል እምነት የለንም። እንዲህ አይነት ሁኔታም ከተፈጠረ ችግሩ የተከተልነው የአደረጃጀት አቅጣጫ ይመስለናል።

## Bibliography


1. UN (1998): Handbook on Civil Registration and Vital Statistics Systems; Preparation of a Legal Framework, Series F, no.71 United Nations, New York, 1998.
2. UN (2001): Principles and Recommendations for a Vital Statistics System, Rev. 2
3. UN (1998): Handbook on Civil Registration and Vital Statistics Systems; Management, Operation, and Maintenance, United Nations, New York, 1998.
4. UN (1998): Handbook Civil Registration and Vital Statistics Systems; Developing Information, Communication and Education, United Nations, New York, 1998.
5. UN (1998): Handbook on Civil Registration and Vital Statistics Systems; Computerization, United Nations, New York, 1998.
6. UN (1998): Handbook on Civil Registration and Vital Statistics Systems; policies and protocols for the release and archiving of individual records, United Nations, New York, 1998.
7. UN (1955): Handbook of Vital Statistics Methods; Studies in Methods... Series F No.7 United Nations, New York, 1991.
8. UN (1964): Principles for a Vital Statistics System, Recommendations for the Improvement and Standardization of Vital Statistics, Series No.19 United Nations, New York, 1964.

9. UN (1991): Handbook of Vital Statistics Systems and Methods, Volume I: Legal, Organizational and Technical Aspects; Studies in Methods Series F No.35, United Nations, New York, 1991.

10. UN (1985): Handbook of Vital Statistics Systems and Methods, Volume II, Review of National Practices, Studies in Methods Series F No.35, United Nations, New York, 1985.

11. IIVRS: Civil Registration and Vital Statistics: A Collection of papers, UNFPA

12. IIVRS: Improving Civil Registration: Editors, Forest E. Linder and Qwao M. Moriyama, 9650 Rockville pike beheads, MD 20814-3998 U.S.A

13. Benjamin Gil: The Kenya Civil Registration Demonstration Project; A Strategy for a Rapidly Developing Country in Africa published by the Department of the Registrar General of Kenya.

14. Collection of papers presented at the African workshop on strategies for accelerating the improvement of civil registration and vital statistics system, Addis Ababa, Ethiopia, 5 to 9 dec. 1994.

15. Organization and status of civil registration in Africa and Recommendations for Improvement, IIVRS Technical paper No.31, April 1988

16. Draft plan of Action for Acceleration the improvement of civil registration and vital statistics systems in the African region, ECA, statistics division.

17.Uses of civil registration and vital statistics in health programmes and services, Dr. oddile frank; world health organization.

18.Uses of vital statistics in demographic analysis, UNECA; population division.

19.Uses of vital statistics for education planning with special reference to south Asian countries, k.s. natarajan UNICEF regional Office for south Asia.

20.Uses of vital statistics in population policy making and evaluation, note by the ESAP Secretariat

21.Uses of vital registration records and statistics for social and economic Development programs, Iwao M.moriyama, International institute for vital registration and statistics.

22.CSA (1995): Report on Experimental Sample Vital Registration in Rural Ethiopia, 1986/87, Addis Ababa.

23.Population and Housing Census Commission Office (2003): National Plan of Action for the Establishment of Civil Registration and Vital Statistics Systems in Ethiopia, Draft.

24. ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት (1995)፤ በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ጥቅምና አስፈላጊነት፣ አደረጃጀትና የመረጃ ፍሰት ሥርዓት (ረቂቅ)፤ አዲስ አበባ፣

25. ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት (1994)፤ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ የመዝጋቢዎች መመሪያ (ረቂቅ)፤ አዲስ አበባ፣

26.ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን (1992)፤ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም፣ አስፈላጊነትና አፈጻጸም (ረቂቅ) አዲስ አበባ፣